በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም እና የኮምንኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረምረቃ መርሐግብር

# የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ

## (ለኢ-አፊ ፊት ተማሪዎች በተዘጋጁት የ7ኛና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጻህፍት ተተኳሪነት)

በ ወይንሸት አሰፋ

ጥቅምት 2016 ዓ.ም.
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
አዲስ አበባ

# የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ

## (ለኢ-አፊ ፈት ተማሪዎች በተዘጋጁት የ7ኛና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጻህፍት ተተኳሪነት)


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት፣ጆርናሊዝምና ኮሚኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የሁለተኛ ዲግሪ (MA) ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ነጥቦች በከፊል ለማሟላት ለአማርኛ ቋንቋና ስነ-ፅሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ ጥናት


የጥናቱ አማካሪ

ጌታሁን አማረ (ፕ/ር)

## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

ይህ **"ለኢ-አፈ ፊት ተማሪዎች የተዘጋጁ የ7ኛና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ"** በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስነሰብ የቋንቋዎች ጥናት የጋዜጠኝነትና የኮምዩኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ ስነ ጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የማስተርስ ዲግሪ ማሟያ በወይንሸት አሰፋ የቀረበው ጥናት የዩኒቨርሲቲውን የጥራትና የወጥነት መስፈርት ስለማሟላቱ በፈታኞች ተረጋግጦ ተፈርሟል፡፡

## የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ -------------------------------------- ፊርማ --------------------- ቀን ------------

የውጪ ፈታኝ ------------------------------- ፊርማ --------------------- ቀን ------------

የውስጥ ፈታኝ ------------------------------ ፊርማ --------------------- ቀን ------------

# የአጥኚዋ ማረጋገጫ

ይህ ‹‹የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ፣ በኦሮሚያ ክልል በ2014ዓ.ም ኢ-አፊ ፊት ለሆኑ የ7ኛና የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጁ የአማርኛ መማሪያ መጻህፍት ተተኳሪነት›› በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሀ ግብር አማርኛ ቋንቋን ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረብኩት ጥናት፣ ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ ወጥ የራሴ ስራ መሆኑን፣ የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ መሆናቸውን በፍርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

የአጥኚዋ ስም ፦ <u>ወይንሸት አሰፋ</u>

ፊርማ ፡ ------------------------------

ቀን ፦ ---------------------------------

# ምስጋና

ከሁሉም አስቀድሜ ይህንን ጥናታዊ ጽሁፍ ጀምሬ እስክጨርስ ድረስ ለረዳኝ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይግባው፡፡ በመቀጠልም ውድ ጊዜያቸውን ሰጥተው በስልክና በኢሜል አድራሻቸው ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ በማረምና በማስተካከል ለረዱኝ ለመምህሬና አማካሪዬ ጌታሁን አማረ (ፕ/ር) የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በመጨረሻም ትምህርቴን እስክጨርስ ድረስ በተለያየ መልኩ ለረዱኝ ለውድ በተሰቦቼና ጓደኞቼ እንዲሁም የጥናቱን ወጪ ለሸፈነልኝ ለአዲስ አበባ  ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬን አቀርባለው፡፡

# የይዘት ማውጫ

**ይዘቶች** **ገጽ**

የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ.......iii
ምስጋና....... v
የይዘት ማውጫ.......vi
የሠንጠረዥ ማውጫ.......ix
አጠቃሎ....... x
ምዕራፍ አንድ....... 1
መግቢያ....... 1
1.1. የጥናቱ ዳራ....... 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት....... 6
1.3. የጥናቱ ዓላማ....... 6
1.3.1. ዓብይ ዓላማ....... 6
1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች....... 7
1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ....... 7
1.5. የጥናቱ ወሰን....... 7
ምዕራፍ ሁለት....... 8
የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት....... 8
2.1. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች....... 8
2.2. ስነ ትምህርታዊ ስዋስው....... 9
2.3. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት....... 10
2.3.1. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ....... 10
2.3.1.1. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ....... 10
2.3.1.2. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ....... 11
2.3.1.3. ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ....... 14
2.3.1.4. ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ....... 15
2.4. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት....... 16
2.4.1. ተገቢነት....... 17

2.4.2. ተከታታይነት ..... 18
2.4.3. ተለጣጣቂነት ..... 18
2.5. የቋንቋ መርሀ ትምህርትና መማሪያ መጻህፍት ..... 18
2.5.1. የቋንቋ መርሀ ትምህርት ..... 18
2.5.2. የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ዓይነቶች ..... 19
2.5.2.1. ሰዋስው ተኮር የመማሪያ መጻህፍት ..... 20
2.5.2.2. ተግባቦት ተኮር የመማሪያ መጻህፍት ..... 20
ምዕራፍ ሦስት ..... 21
የአጠናን ዘዴ ..... 21
3.1. የምርምሩ ስልት ..... 21
3.2. የጥናቱ የመረጃ ምንጭ ..... 21
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ..... 21
3.3.1. የሰነድ ፍተሻ ..... 21
3.3.2. ቃለ መጠየቅ ..... 22
3.3.3 የጽሁፍ መጠየቅ ..... 22
3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ ..... 22
ምዕራፍ አራት ..... 23
የመረጃዎች ትንተና የውጤት ማብራሪያ ..... 23
4.1. የመረጃዎች ትንተና ..... 23
4.2. በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ..... 25
4.2.1. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ..... 25
4.2.2. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ ..... 28
4.2.3. ውጤት ተኮር አቀራረብ ..... 33
4.2.4. ሂደት ተኮር አቀራረብ ..... 35
4.3. በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት ..... 37
4.3.1. ተገቢነት ..... 37
4.3.2. ተከታታይነት ..... 38
4.3.3.ተለጣጣቂነት ..... 40
4.4. መማሪያ መጻህፍቱ ከመረሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸው ዝምድና ..... 41

ምዕራፍ አምስት ........ 44
ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳብ ........ 44
5.1. ማጠቃለያ ........ 44
5.2. የመፍትሄ ሐሳብ ........ 46
ዋቢ ጽሁፎች ........ 47
አባሪዎች ........ 50
አባሪ -1 ፦ ለተማሪዎች  የተዘጋጀ የፅሁፍ መጠይቅ ........ 50
አባሪ 2 ፦ ለመምህራን የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ ........ 52

## የሠንጠረዥ ማውጫ


ሰንጠረዥ-1፡ የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ አጠቃላይ ቅኝት ...................... 24

ሰንጠረዥ-2፡ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አጠቃላይ ቅኝት ................................................ 25

ሠንጠረዥ-3፡ ቅድመና ድህረ ግንድ ቅጥያን መለየት ........................................................ 30

ሠንጠረዥ-4፡ ስምና የስም ገላጭቃላትን መለየት................................................................ 31

ሠንጠረዥ-5፡ ስምና የስም ገላጭ የሆኑትን መለየት .......................................................... 34

ሠንጠረዥ-6፡ አያያዥ ቃላት በመጠቀም ነጠላ ዐረፍተነገሮችን ወደ ድርብ ዐረፍነገሮች መቀየር ........................................................................................................... 36

ሠንጠረዥ-7፡ የ7ኛ ክፍል በመማሪያ መፅሀፍና በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት ዝርዝር የሰዋስው ይዘቶች ............................................................................................. 41

ሠንጠረዥ- 8፡ የ8ኛ ክፍል በመማሪያ መፅሀፍና በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት ዝርዝር የሰዋስው ይዘቶች ............................................................................................. 42

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት በኦሮሚያ ክልል በ2014ዓ.ም ኢ-አፊ ፊት ለሆኑ የ7ኛና የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት የሚፈትሽ ነው። ጥናቱ ጥያቄ አድረጎ በተነሳባቸው ነጥቦች ዙሪያ የቋንቋ ምሁራን ያቀርቧቸውን ንድፈ ሀሳባዊ መሠረቶች መንደርደሪያ በማድረግ በሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት መርሃ ስር መነሳት ያለባቸውን ነጥቦች ለመመለከት ሞክሯል። የጥናቱ ዓብይ የመረጃ ምንጭ የሰነድ ፍተሻ ሆኖ ከተማሪዎችበፅሁፍ መጠይቅና ከመምህራን በቃለ መጠይቅ በተገኙ ምላሾችምመረጃውን ለማጠናከር ተሞክሯል ። ከዚህ የመረጃ ምንጮች የተገኙ ምላሾችም ባላቸው ተዛማጅነት አንድ ላይ እየተደራጁ በምዕራፍ አራት ስር ተተንትነዋል። ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው ከይዘቶች አቀራረብ አንጻር የ7ኛና የ8ኛክፍል ውጤት ተኮር አቀራረብን ሰፊ ሽፋን የሰጠ ሲሆን የ7ኛና የ8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ላይ የበለጠ ትኩረት በመስጠት አብላጫውን ሽፋን እንዲይዙ በማድረግ የቀረቡ ናቸው።ከተገቢነት አንፃርም በአብዛኛው መፃህፍቱ ለተዘጋጁላቸው ተማሪዎች ዳራዊ እውቀት፣የመስራት አቅም፣የመረዳት ችሎታ ተገቢ ያልሆኑ ቸግሮች እንዳሉባቸው ለማስተዋል ተችለዋል።ከአደረጃጀት አንፃርም በ7ኛና 8ኛ ክፍል መማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አብዛኞቹ ተደጋግመው የቀረቡ እንዳልሆኑና ጥልቀታቸውም እየጨመረ የመሄድ ችግር ያለባቸው እንዳሉ ተስተውሏል፡ ፡ በሁለቱም መማሪያ መፃህፍት መካከል ተለጣጣቂነት የሚታይባቸው ይዘቶችም እንዳሉ ሁሉ የተወሰኑት ስፋትና ጥልቀታቸው እየጨመረ የማይሄዱ ይዘቶች እንዳሉ ለማየት ተችሏል።

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ዋናውን ሚና ከሚጫወቱ የትምህርት መሣሪያዎች ውስጥ መማሪያ መፃህፍት ዋና ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በትምህርት ቤቶች ውስጥ በሚተገበር የትምህርት አሰጣጥ ስልት መማሪያ መፃህፍት ግንባር ቀደምት የእውቀት ማስተላለፊያ መሳሪያዎች ሆነው ያገለግላሉ፡፡ የቋንቋ መማሪያ መፃህፍት በጥንቃቄ የተመረጡና የተደራጁ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ለተማሪዎች ማቅረብ ይችሉ ዘንድ በዝግጅት ወቅት የተለያዩ ስነልሳናዊ፣ ስነ ትምህርታዊና ስነልቦናዊ ንድፈ ሀሳቦችን እና መርሀ ትምህርትን መሠረት እንዲያደርግ ይመክራል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዝግጅት ወቅትም ይሁን በሥራ ላይ ከዋሉ በኋላ ተከታታይ ግምገማ ሊደረግባቸውና ከዚህም በሚገኙ መጋቤ ምላሾች ሊሻሻሉ እንደሚገባ Cunningsworth (1995:12) ይገልፃሉ፡

የቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ስርዓት ባለው መንገድ በቋንቋ እንዲጠቀሙ ማስቻል ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማ የቋንቋ ክህሎችን ማጎልበት እና የስነልሳንና ስነፅሁፍ እውቀትን ማስጨበጥ ነው፡፡ ይህንን መተግበር ይቻል ዘንድ ብቃት ያላቸው የቋንቋ ማስተማሪያ መጻህፍት በወጉ ማሰናዳት ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎች ሥርዓት ባለው መንገድ በቋንቋ መገልገል ይችሉ ዘንድ በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ከሚካተቱት የክሂልና የስነፅሁፍ ይዘቶች በተጨማሪ የሰዋስው

ትምህርት አንዱ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ሰዋስው ቋንቋ ትምህርት የትኩረት አቅጣጫ አንድ መስክ መሆኑን ያስገነዝበናል፡፡

በርግጥ እንደ Bygate,M Tonkyn, A ,Williams, E (1994) ገለጻ የሰዋስው ትምህርት ዘርፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን ስፍራ በተመለከተ ከአፍ መፍቻ ወይም ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር በተያያዘ መልኩ በትምህርትነት መሰጠት ‹‹አለበት ወይም የለበትም›› በሚል ረገድ ብዙ ክርክሮች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ይሁን እንጂ የሰዋስው ትምህርት በሁለተኛ ወይም ውጪ ትምህርት ውስጥ የትምህርቱ አብይ ጉዳይ ሆኖ ከመገኘት ያገደው ነገር የለም፡፡ ሰዋስው ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ በርካታ ምሁራን የተለያየ ፍቺ ሰጥተዋል፡፡

ለምሳሌ፡ Ur (1991፡75) ሰዋስው ትክክለኛ ዓረፍተነገር ለመመስረት ቃላትን መደርደር ማለት ነው፡፡ Mitchell(1994)፣Ruthford (1987)እና Tonkyn (1994) እንደምያስረዱት በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ለአፍ መፍቻ ቋንቋ ትኩረት የተሰጠበት ቢሆንም በተለይም እስከ 1980ዎቹ ድረስ የሰዋስው ትምህርት የቋንቋ ትምህርት ማዕከላዊ ጉዳይ ሊሆን መቻሉን ይጠቁማሉ፡፡ ይህም የሆነው ያለምክንያት አይደለም፡፡የሰዋስው ትምህርት ለአጠቃላይ የቋንቋ ትምህርት ጉልህ ሚና ስላለው እንጂ፡፡ ባየ (1987፡10) ይህንኑ ጉዳይ ፣የቋንቋ ትምህርት በተመለከተ በርግጠኝነት መናገር ከምንችልባቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ‹‹የአንድን ቋንቋ አጠቃቀሙን ማለትም ክሂሎቱን ከእነስርዓቱ የተገናዘበ ተማሪ የተሻለ እውቀት ያለው መሆኑን ነው ›› በማለት የስነልሳን ትምህርት የክሂል ትምህርትን ያህል የሚያስፈልግ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

ጌታሁን (1990) በበኩላቸው የሰዋስው ትምህርት ዘመናዊ እሳቤ ህግጋትን የማወቅና ያለማወቅ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ከዚያ ባሻገር ያለውንና ለተግባቦታዊ ተግባር የሚሰጠውን ፋይዳ ከግንዛቤ ያስገባ መሆን እንዳለበት አፅንኦት ሰጥተው ይገልፃሉ፡፡

Palmer (1984) እንዲሁ የሰዋስው ትምህርት ትኩረት ተማሪዎች በቋንቋው ሰዋስዋዊ እውቀት ላይ የተመሠረተ የተግባቦት ብቃት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው በማለት ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን መሠረታዊ ቦታ አስረግጠው ይናገራሉ፡፡ ሁሉም ቋንቋዎች የየራሳቸው ሰዋስው አላቸው ለሚለው በማንኛውም ቋንቋ የሚገኝ ሰዋስው ስለ ድምፅ፣ ስለ ቃላት ትርጉም ፣ ስለ ሐረግ መዋቅር ስርዓታዊና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያስተምርነው ፡፡

ባየ (2000) እና Brown (1994) ሰዋስው አንድን ቋንቋ ከድምፅ ቅንጅት እስከ ሀረግ ምስረታ ያለውን ስርዓት የሚያጠና ነው፡፡ ይህም ማለት ስርአቱን መሰረት ያደረገው የቋንቋውን ተናጋሪዎች ስምምነት ወይም ተናጋሪዎቹ በአጠቃቀም ወቅት ትክክል ወይም ስህተት ለማለት የሚያስችላቸው ነው፡፡ ትኩረቱ በቋንቋ ቅርፅ ላይ ብቻ ሳይሆን ተግባቦትን የሚመለከት መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

ሰዋስው ሰፊ እሳቤ ያለው ሲሆን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ ያለውና ቋንቋን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያጠናና ትክክለኛውን የዓረፍተነገር አወቃቀር ስርዓት እዲጠቀሙና ተግባቦትን እንዲከውኑ ማስቻል ነው፡፡

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ሥርዓት በሚገባ ተረድተው በትክክለኛ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ የሚያስችል መሆን አለባቸው፡፡ ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ ትምህርቱ የቋንቋውን ቅርፅ፣ፍቺና አጠቃቀም አስተሳስሮ መቅረብ እንደሚገባ Larsen-Freemn(1986) ይገልፃሉ፡፡በተጨማሪም እነዚህን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ታሳቢ ያደረገ ትምህርት ለማቅረብ በመጀመሪያ የታላሚውን ቋንቋ ሥርዓት መሠረት በማድረግ ተገቢ የማስተማር ሥነ-ዘዴን መምረጥ እንደሚያስፈልግና የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚገባ ለመቆጣጠር የሚያስችል ተገቢ የይዘት አመራረጥ ፣አቀራረብና አደረጃጀት መከተል እንዲሁም ከቋንቋው ጋር የሚገኙ መልመጃዎችንና ተግባራትን በምሳሌዎችና

በማብራሪያዎች አስደግፎ ማቅረብ እንደሚያስፈልግም  ያስረዳሉ፡፡ በማህበራዊ ተራክቦ የአንድን ቋንቋ ሥርዓት  ጠብቆ ለመግባባት መሰረታዊ የቋንቋ ክህሎችንና የሰዋስው ህጎችን ማወቅ ያለው ጠቀሜታ ከፍተኛ መሆኑ የማይካድ ሀቅ ነው፡፡

Ur (1988፡4-5) በአንድ ቋንቋ የሰዋስው ችሎታ ወይም አጠቃቀሙን በአግባቡ ለይተን ካላወቅን የቋንቋ ችሎታችን ደካማ ወይም ጎዶሎ እነደሚሆን አያጠያይቅም ሲሉ ገልፀዋል፡፡

ከገለፃው መረዳት እንደሚቻለው ሰዋስው በአንድ ቋንቋ ውስጥ ሰፊ ቦታ ያለው ሲሆን ይህም በትምህርት ቤት ደረጃ በሚሰጥ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ሁለተኛ ቋንቋና የውጭ ቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋስውን ማስተማር ጠቀሜታ እንዳለው ይጠቁማል፡፡ ከዚሁ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ጌታሁን (1989፡V) ‹‹ የቋንቋ ትምህርት አላማ ትኩረት በክሂሎች ላይ ብቻ ሳይሆን በሰዋስውም ላይ መሆን አለበት ፡፡ምክንያቱም ሁለቱም አንድን ቋንቋ ተማርኩ ከሚል ሰው የሚጠበቁ ችሎታዎች ናቸው፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ ተምረያለው የሚለው ሰው ዕውቀት ቁንፅል ይሆናል፡፡›› በማለት ገልፀዋል፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውን የሰዋስውን ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት ስንመለከት የግምገማው ዋነኛ ትኩረት አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች በተዘጋጀው የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሀፍት የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ ላይ ነው፡፡ በየክፍል ደረጃው የሚዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የየራሳቸው የሆነ ስህተት ያጋጥማቸዋል፡፡ ስለዚህ በየክልሉ የሚዘጋጁት መማሪያ መጻህፍት የተማሪዎቹን የእውቀት ዳራና ነባራዊ ሁኔታ ያማከለ ይሆኑ ዘንድ ተከታታይ ግምገማ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

ይህንንም Dubin and Olshtain (1986:2-3) እና Cunningsworth (1984:5) መማሪያ መጻህፍት ተዘጋጅተው ስራ ላይ ከዋሉ በኋላ ተከታታይ ግምገማ ሊደረግባቸው እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡ ስለሆነም ይህ ጥናት ለኦሮሚያ ክልል የተዘጋጀውን የ7ኛና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መጻህፍት ከሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት አንፃር ምን እንደሚመስል ገምግሟል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት ትኩረት በኦሮሚያ ክልል ለኢ-አፊ ፊት የተዘጋጁ የ7ኛና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረባቸውና አደረጃጀታቸው ምን ይመስላሉ? እንዴትስ ተዋቅረዋል? የሚለውን ጥያቄ መመርመር ነው፡፡ በተተኳሪው መጻህፍት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀትን አስመልክቶ የተደረጉ ጥናቶች ቢኖሩም በክልሉም ሆነ በትምህርት ቤቱ በ2014ዓ.ም ተዘጋጅቶ በ2015ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው መፅሀፍ ላይ የተደረገ ጥናት ባለመኖሩ፣ ጥናቱን ለማድረግ አነሳሽ ምክንያት ሆኗል፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

ጥናቱ ሁለት ዓላማዎች አሉት- ዓብይ ዓላማና ዝርዝር ዓላማዎች፡፡

### 1.3.1. ዓብይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልል በ2015ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው የ7ኛና የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እደሚመስል መፈተሽ ነው፡፡ ይህን አጠቃላይ ዓላማ መነሻ በማድረግም ለሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች መልስ ለመስጠት ሞክሯል፡፡

### 1.3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- ይዘቶቹ የቀረቡበትንና የተደራጁበትን መንገድ መተንተንና ጠንካራና ደካማ ጎኖቹንም መለየት
- የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አስመልክቶ በማስተማሪያ መፅሀፍና በመርሃ ትምህርቱ መካከል ያለው ትስስርና ዝምድና መፈተሽ፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

በቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ከሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች መካከል አንዱ የሰዋስው ትምህርት ነው፡፡በመሆኑም በታላሚው መጻህፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት መገምገም የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

- በሰዋስው ትምህርት ከይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ረገድ በተተኳሪው መጻህፍት ውስጥ የታዩትን ጠንካራና ደካማ ጎኑ ደግሞ የሚሻሻልበትን አቅጣጫ ለቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ አዘጋጆች ይጠቁማል፡፡
- በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረበውን ትምህርት አቀራረብና አደረጃጀት በመፈተሽ ምን አይነት ገፅታ እንዳለው ለደረጃው መምህራን ፍንጭ ይሰጣል፡፡
- ቀጣይ ከዚህ ርዕስ ጋር ተዛማጂ የሆነ ጥናት ለሚያደርጉ አካላት የመነሻ ሀሳብ ይሰጣቸዋል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

በተተኳሪው መጻህፍት ውስጥ የተነሱት ርዕሰ ጉዳዮች በርካታ ቢሆኑም ይህ ጥናት ትኩረት ያደረገው በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልል በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው የ7ኛና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ብቻ ለደረጃው ከተዘጋጀ መርሀ ትምህርት ጋር አያይዞ የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ ሌሎች የትምህርት ይዘቶችን አይመለከትም፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት

## 2.1. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች

የሰዋስው ትምህርት ትኩረት በቋንቋው ቅርጽና መዋቅር ላይ ሆኖ መምህር መር የትምህርት ሂደትን በመከተል ተማሪዎች በሚሰጣቸው ገለጻና ማብራሪያ የቋንቋውን ህግጋት በሙሉ እንዲቆጣጠሩ ማድረግ ነበር፡፡የተማሪዎች የቋንቋ ብቃት ተደርጎ የሚታየውም ቃላትን በተገቢው ቦታቸው በመሰካት ዓረፍተ ነገሮችን ማዋቀር መቻላቸው ነው፡፡ ለዚህም ሰዋስው የትርጉም ዘዴን እንደምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ይህን የማስተማር ስነዘዴ መሠረት አድርገው በሚዘገጁ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚቀርቡት መልመጃዎችም በቋንቋው ቅርጽና ህግ ላይ ያተኮሩ ሆነው በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚተው ቦታ መሙላትን፣በታላሚው ቋንቋ የተጻፉ ዓረፍተ ነገሮችን ወደ መፍቻ ቋንቋ መተርጎምና የቃላትን ቅደም ተከተል ማስተካከል የመሳሰሉ ይዘቶች ነበሩ Nunan (1991) ፡፡

Palmer (1984) እንደሚሉት የሰዋስው ትምህርት ትኩረት ተማሪዎች በቋንቋው ሰዋስዋዊ እውቀት ላይ የተመሰረተ የተግባቦት ብቃት እንድኖራቸው ማስቻል ነው፡፡ ተማሪዎች የቋንቋውን ቅርጽ ከፍቺና ከአጠቃቀም ጋር አጣምረው በመማር ተገቢ የሆኑ ዓረፍተነገሮችን አፍልቀው እንዲጻፉ ወይም እንዲናገሩ አዳምጠው ወይም አንብበው መልዕክትን እንዲጨብጡ የሚያስችል የትምህርት ሂደትን የሚከተል መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ፡፡

Ellis (2000) ይህንኑ ሃሳብ ስያጠናክሩ የሰዋስው ትምህርት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ባህሪያት በሚገባ ተረደተው በተግባቦት ሂደት ጥቅም ላይ የሚያውሉበትን ሥርዓት የሚያሳይ እንደመሆኑ ሰዋስውና ተግባቦት ተነጣጥለው መታየት የለባቸውም ይላሉ፡፡ ምክንያቱም አንድ የቋንቋ ቅርጽ የያዘውን ቃላዊም ሆነ ሰዋስዋዊ ፍቺ መገንዘብ ለተግባቦቱ

የሚሰጠውን ቅልጥፍና መገመት አያዳግትም፡፡ ስለዚህ የሰዋስው ትምህርት ለቋንቋው ቅርጽ፣ ፍቺና አጠቃቀም ትኩረት መስጠት አለበት ይላሉ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ምሁራኑ ካቀረቡት ገለጻ መረዳት እንደሚቻለው ቅርጽ፣ፍቺና አጠቃቀም በሰዋስው ትምህርት ውስጥ ትኩረት ሊያገኙ እነደሚገባና ተነጣጥለው የማየታዩ መሆኑን ነው፡፡ ቅርጽ ካለ ፍች መኖሩ የግድ ነው፡፡ፍች ካለም ቅርጽመኖሩ የግድ ነው፡፡ አጠቃቀምም እንዲሁ ከቅርጽና ከፍች ጋር የተሳሰረ ነው፡፡ እነዚህ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተቆራኙና ለትምህርቱ ዓላማ ግብ መምታት ተመጣጣኝ ያላቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ገሩዚህም

## 2.2. ስነ ትምህርታዊ ስዋስው

ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ለመማር ማስተማር ዓላማ አዘጋጅቶ የያዘ የሰዋስው ጽሁፍ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይባላል፡፡ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦችን ከሚያራምዱ የሰዋስው ዓይነቶች (አዛዥ ሰዋስው) ሳይቀር ለመማር ማስተማሩ ጠቃሚ ግብዓቶችን በመውሰድ ለትምህርቱ ዓላማ ቃኝቶ ያቀርባል እንጂ አንድን ንድፈ ሀሳብ ወይም ሰዋስው እሳቤ አያራምድም፡፡ በመሆኑም ስነ ትምህርታዊ ሰዋሰው የተግባቦት ብቃትን ከሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ጋር አጣምሮ ቋንቋን ለማስተማር የሚያገለግል፤ የስነ ትምህርት፣ የስነ ልቦናና ሥነ ልሳን መሠረት ያለው፣የተማሪውን ሁኔታ ያገናዘበ የአቀራረብ ሥልትን ታሳቢ የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህ ባህሪውም የታላሚውን ቋንቋ የሰዋስው ሥርዓት እውቀት የመጨረሻ ግቡ ሳያደርግ ሰዋስዋዊ ስርዓቱ ተግባራዊ አገልግሎት እንዲኖረው ተግባቦታዊ ልምምድ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ይህን አስመልክተው Nunan (1991:153) ሲገልጹ ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው ተማሪዎች ስለ ታላሚው ቋንቋ ጠለቅ ያለ እውቀት እንዲኖራቸው ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶችን በአውድ ውስጥም እንዲያገኙ በማመቻቸት ተጨባጭ በሆነ ልምድ በመታገዝ የቋንቋውን ቅርጽና ፍቺ በአገልግሎት ውስጥ እንዲጠቀሙ የሚያስችል መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ይህም ስነ ትምህርታዊ

ሰዋስው በመማር ማስተማሩ ሂደት ለተማሪዎች የሰዋስው ዓይነቶች በተሻለ መልኩ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት የሚያመለክት ሲሆን ይህንን የሰዋስው ዓይነት የተለየ የሚያስብሉ መገለጫ ባህሪያት እንዳሉ Greenbaun (1986) ይገልፃሉ፡፡ እነዚህ ባህሪያትም ስነ ትምህርታዊ ሰዋስው የትምህርት ይዘቶችን ርዝመት በየክፍል ደረጃው በመወሰን ያቀርባል፡፡የሥነ ልቦናዊ ስነ ልሳን መሠረትነት ያለው በመሆኑ ለተማሪዎች ተገቢውን ትኩረት ይሰጣል፡፡

የሰዋስው ትምህርት ይዘት ገለፃዎች፣ምሳሌዎችንና መልመጃዎች በየደረጃቸው ተመጥነው እንዲቀርቡ ያግዛል ፡፡ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት ትኩረት ሰጥተው እንዲማሩ ያደርጋል፡፡ በተግባር ሊተረጉመው የሚችሉ ይዘቶችን በማቅረብ ተማሪዎችን ለተግባራዊ ልምምድ እንዲነሳሱ ያደርጋል፣ የሚሉ ናቸው፡፡ ለዚህ ጥናትም መሰረት የተደረገው ይኸው የሰዋስው ዓይነት በመሆኑ በመፃህፍቱ የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች የሚገመገሙት በስነ ትምህርታዊ ሰዋስው እሳቤ ነው፡፡

## 2.3. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት

### 2.3.1. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ አስመልክቶ ከሚነሱ ነጥቦች መካከል በዚህ ጥናት ውስጥ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ፣ሂደት ተኮርና ውጤት ተኮር የሚሉት ተተኳሪ ይሆናሉ፡፡

#### 2.3.1.1. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ስልት ትኩረት የሚያደርገው ዝርዝር የቋንቋ ባህሪያትን የሚያሳዩ ምሳሌዎችና መልመጃዎች አጥኚው ከተገነዘቡና ከሰሩ በኋላ አጠቃላይ የቋንቋውን ሥርዓት እንዲረዱ የሚያደርግ ነው፡፡ Woods (1995፡76) ከዝርዝር ወደ አጠቃይ ማቅረብ ማለት በአግባቡ የተመረጡ ምሳሌዎች በማቅረብ ተማሪዎች የቀረቡትን ምሳሌዎች መሠረት አድርገው የተሰጣቸውን መልመጃዎች ከሰሩ በኋላ የቋንቋውን ህግ በራሳቸው እንዲደርሱበት የሚያደርግ

አካሄድ የተከተለ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡በመሆኑም የአቀራረብ ስልቱ ተማሪዎቹ ከቋንቋው ዝርዝር ተነስተው አጠቃላይ ወደሆነው የቋንቋ ህግ እንድሸጋገሩ የሚያስችል አካሄድን የሚከተል መሆኑን Larsen-Freeman(1991) ይጠቁማሉ፡፡ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚደረግ የሰዋሰው ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች ስለ ቋንቋው ህግ በቀጥታ ከመማራቸው በፊት ከቀረቡት ምሳሌዎች ተነስተው በራሳቸው የመረዳት አቅም የቋንቋውን ህግ ሊያውቁ የሚችሉበት የትምህርት አቀራረብ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ የአቀራረብ ስልት መሠረት የቋንቋ ሰዋሰዋዊ ህጎች በቀጥታ ለተማሪዎች አይቀርቡም ፡፡ይህ አደረጃጀት ተማሪዎች የሰዋሰው ህግ ሳይነገራቸው የተለያየ ዓረፍተ ነገሮችን ይተዋወቃሉ፣ይሰራሉ፡፡ራሳቸው ወደ አጠቃላይ ህግ በመጨረሻ ይደርሳሉ ተብሎ ይጠበቃል ይላሉ፡፡Nunan(1991፡27-29)፡፡

ማረው (2003፡43) ሆፐኪሰን (2002) ን ጠቅሶ እንደገለፀው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ሰዋስው የማስተማር ዘዴ የሚማሩ ተማሪዎች በመጀመሪያ መረጃው ውስጥ ነው እንዲገቡ የሚደረጉት፣ከዚያም ተናጠላዊ መረጃዎች በውል በማስተዋል እንደየተዛምዷቸው ዓይነት በዓይነት ያደራጁቸዋል፡፡ በመቀጠል መረጃዎቹን መሠረት በማድረግ መላምት ይነድፋሉ፤ ውጤትንም ይተነብያሉ፤ ይህንንም በማረጋገጥ ወደ ማጠቃለያ ይደርሳሉ፡፡ እናም ስለ አቀራረቡ በነገሮች መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ለመረዳት፣ተግባራዊ የሆነ እውቀትን ለመገንባትና ስለ ነገሮች በስፋትና በጥልቀት ለማሰብ እንድችሉ ጠንካራ መሠረት ይጥልላቸዋል በማለት ያብራራል፡፡

### 2.3.1.2. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ

በዚህ ስልት ተማሪዎች ስለሚማሩት ቋንቋ ህጋጋት የሚያሳይ ገለፃ ይቀርብላቸዋል፡፡ከገለፃው በመነሳትም ህጋጋቱን ለመተግበር ወይም ለተግባቦት ለማዋል ይሞክራሉ፡፡ ይህም መሆኑ ተማሪዎች የቋንቋውን ህጋጋት በፍጥነትና በቀላሉ እንዲረዷቸው ያስችላቸዋል፡፡ሆኖም ይህ

ብቻውን በቂ አይሆንም። ምክንያቱም ተማሪዎች በገለፃ ብቻ በመታገዝ ህግጋቱን በጥቅም ላይ ወይም ለተግባቦት ማዋሉ አዳጋች ሊሆንባቸው ይችላል። ስለዚህ ገለፃው በበቂ ምሳሌዎች ተደግፎ ሊቀርብ ይገባል ይላል (Cunningsworth (1995) ።

ይህ ስነ አቀራረብ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ መልኩ ህግን፣ መመሪያን፣ፅንሰ ሀሳብን እና ንድፈ ሐሳብን በመግለፅ ለማስተማር የሚሞክር ስነ አቀራረብ ሆኖ በቅድሚያ የቋንቋውን ህግ ነግሮ፤ምሳሌ በመስጠት ሌሎች ተመሳሳይ ስራዎችን እንድሰሩ የሚያደርግ ስለሆነ አቀራረቡም አእምሮዓዊ ነው። በተጨማሪም በቀረበላቸው ምሳሌና በተሰጣቸው ህግ መሰረት ሌሎች ተመሳሳይ መልመጃዎችን በቃልና በፅሁፍ እንዲለማመዱ ማድረግ ነው። እንድሁም የሰዋስው እውቀት ለምን ተግባር እንደሚውል እንብዛም ትኩረት ባይሰጥም የሰዋስው ትምህርት አይቀሬ ስለሆነ ይህን ስነ አቀረቀረብ መጠቀም ጠቃሚ ነው።

Harmer (1987) እና Larsen-Freeman (1991) ይህን የአደረጃጀት ስልትን አስመልክቶ ከላይ ከቀረበው ገለፃ ጋር ተመሳሳይ ገለፃ ሰጥተዋል።በዚህ አቀራረብ ስልት ለተማሪዎች ስለታላሚው ቋንቋ ህግጋት የሚያሳይ ገለፃ ይቀርብላቸዋል። ገለፃውንም መሠረት በማድረግ ህግጋቱን በዝርዝር መለማመድ ይቀጥላሉ። ይህ አቀራረብ ለትምህርት የቀረቡትን ይዘቶች በማብራራት ስለሚጀምር በትምህርት ሂደት ውስጥ ለመምህሩ ሰፊ እድል ስለሚሰጥ የተማሪዎችን ተሳትፎ መስተጋብር የሚገድብ ነው። ይህ ደግሞ ደካማ ጎኑን የሚያሳይ ሲሆን ተማሪዎቹ የታላሚውን ቋንቋ ህግ በቀላሉ እንዲረዱና ህጉን ተከትለው ተግባቦትን እንዲተገብሩ ማድረጉ ጠንካራ ጎኑን ያሳያል።

ከላይ በዝርዝር ለማየት እንደተሞከረው ሁለቱም የአቀራረብ ስልቶች የየራሳቸው ጥንካሬና ድክመት ይታይባቸዋል።በተለይም አንዱ አቀራረብ የሌላኛው ግልባጭ ከመሆኑ የተነሳ የአንዱ ጥንካሬ የሌላው ድክመት ሆኖ ታይቷል። በመሆኑም አንደኛው የሌላኛውን ክፍተት የሚሞላ

መሆኑን ተገንዝቦ እንደ አስፈላጊነታቸው ሁለቱንም አቀራረቦች እያፈራረቁ ጥቅም ላይ ማዋል ይገባል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ክፍል ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች የተለያዩ እንደመሆናቸው መጠን የተለያየ የትምህርት አቀባበል ችሎታ፣የመማር ስልት ምርጫ ወዘተ ያላቸው መሆናቸውም ልብ ሊባል ይገባል፡፡ይህም ብቻ ሳይሆን በተለያዩ የትምህርት አላማዎች፣የተለያየ የአቀራረብ ስልቶችን የሚከተሉ ከመሆናቸው የተነሳ እነዚህንና መሰል ሁኔታዎችን ለማሻሻል እንደየሁኔታው ሁለቱንም የአቀራረብ መርሆዎችን በተገቢው ሁኔታ እያፈራረቁ መጠቀም የሚያስፈልግ መሆኑን Harmer (1991)ያስገነዝባል፡፡

Thorn Bury (1999፡32) እንደገለፁት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ሰዋስው የማስተማር ይዘቶች አቀራረብ ስንከተል የሚከተሉትን መመሪያዎችን ማስተዋል እንዳለብን ይገልፃሉ፡፡ እነሱም፡-

- የሰዋስው ህጎች የግድ እውነተኛ መሆን፣
- የሰዋስው ህግ ውስንነት እንዳለው በግልፅ ማሳየት ፣
- የሰዋስው ህጎችን ግልፅ እንዲሆኑ ይፈልጋል፣
- የሰዋስው ህጉ ቀለል ያለ መሆን አለበት ፣
- የሚቀርበው የሰዋስው ህግ የተማሪዎችን እውቀት ያገናዘበ መሆን አለበት፣

በአጠቃላይ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ሰዋስው የማስተማር አደረጃጀትን ስንከተል ገለፃው በምሳሌ መደገፍ አለበት፡፡ እንዲሁም አጭር፣ተማሪዎችን የሚያሳትፉ እና ህጎችን ከራሳቸው ጋር እንዲያዋህዱ የሚያደርጉ መሆን አለባቸው፡፡

### 2.3.1.3. ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ስልት መሠረት የሚያደርገው በታላሚው ቋንቋ መዋቅር ዙሪያ ባለው የቋንቋ ቅርጽ ላይ መሆኑን፣Batstone (1994፡51) ይገልጻሉ፡፡ይህም ማለት ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ሥርዓት ላይ በማተኮር የቃላትና የዓረፍተነገር አመሰራረት እውቀት እንዲኖራቸው ማድረግን ትኩረት ያደረገ የአቀራረብ ዘዴን የሚከተል ነው፡፡ በመሆኑም ስልቱ ተማሪዎቹ የሰዋስው አሃዶችን ነጥለው በመተንተን በቋንቋው ዝርዝር ህግ ላይ ተመስርተው ትክክለኛ ዓረፍተ ነገሮችን እንዲያፈልቁ የሚያስችላቸው ነው፡፡ ይሁን እንጂ የአቀራረብ ስልቱ ልማዳዊ የሆነ የሰዋስው ትምህርት የአቀራረብ መርህን የተከተለ፣በመጻህፍት ላይ የተመሠረተና በቋንቋ መዋቅራዊ ህግጋትና ብያኔዎች ላይ ያተኮረ ሲሆን በዘዴው የሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ዓላማ ተግባቦት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ተማሪዎች የቋንቋውን ቃላት በቃል ክፍላቸው እንዲለዩ፣ቃላትን፣ሀረጋትንና ዓረፍተ ነገሮችን በተናጠል እንዲተነትኑ እና

እንዲመሠርቱ የሚያደርግ እንጂ እነዚህን ቅርጾች ከተግባቦት ጋር በማቀናጀት እንዲለማመዷቸው የሚያስችል አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ግን ለማስተማር ሥራ ፈጣን መሆኑ፣ ለመምህሩ ትምህርት አሰጣጥ ቀላልና ምቹ መሆኑ ደግሞ ከጠንካራ ጎኑ የሚጠቀሱት ናቸው፡፡

Harmer (1991) እና Batsone (1994) የአቀራረብ ስልቱን ጥንካሬና ድክመት በሚከተለው መልኩ አስፍረውታል፡፡

- ግብዓቶችን መርጦና አደራጅቶ ማቅረብ፣
- ውስን ዓላማ ይዞ የተማሪውን ልምምድ በተወሰነ ቅርጽ ላይ መገደብና
- የጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ማስጨበጡ ከጠንካራ ጎኖቹ የሚጠቀሱት ስሆኑ፣
- ይዘቶችን በመምረጥናበማደራጀት ሂደት የተማሪውን ፍላጎት መሠረት ያለማድረጉ፣
- ለቅርጽ እንጂ ለፍቺ ትኩረት ያለመስጠቱና
- ድርጊታዊ የማስተማሪያ ስልትን ያለመጠቀሙ ደግሞ ደካማ ጎኖቹ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

### 2.3.1.4. ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ

ይህ የአቀራረብ ስልት የውጤት ተኮር ተቃራኒ ነው፡፡ዓላማው ሰዋስውን ለተግባቦታዊ አገልግሎት ማዋልን የሚመለከት ነው፡፡ Batsone(1994፡51) እንደ ገለጸው ሂደት ተኮር የአቀራረብ ስልት ተማሪዎች በቋንቋው ይበልጥ እንዲጎለብቱ፣ማለትም በአውድ ውስጥ ትርጉም ሰጪ የሃሳብ ልውውጥ እንድያደርጉ በማድረግ የቋንቋውን ቅርጾች ይበልጥ እንዲጠቀሙባቸው የሚያስችል አቀራረብ መሆኑንም ነው፡፡ ከዚህ የምንረዳው ስልቱ ተማሪዎቹ በራሳቸው አውዶች ማለትም ከራሳቸው ገጠመኝ ፣ዳራዊ እውቀት በመነሳት ሰዋሰዋዊ ህግጋትን በራሳቸው ጥረት እንዲገነዘቧቸው የሚያደርግ አካሄድን የሚከተል መሆኑን ነው፡፡

ይህ ስልት እንደ ሌሎቹ ሁሉ የራሱ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት፡፡ ከጠንካራ ጎኖቹ መካከል በጉልህነት የሚጠቀሱት ተማሪዎቹ የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ የታላሚውን ቋንቋ

መዋቅራዊ ፍቺና አጠቃቀም ተገንዝበው በቋንቋው መገልገል እንዲችሉ ማድረግ ሲሆን ፣ ከደካማ ጎኖቹ መካከልም፡-

- ለፍቺ ብቻ እንጂ ለቅርጽ ትኩረት ያለመስጠቱ፣
- ሰዋሰዋዊ ስርዓቶችን ለተማሪዎቹ መርጦና አደራጅቶ ያለማቅረብ፣
- ውስን ዓላማ ይዞ የተማሪዎችን ልምምድ በተወሰነ የቋንቋ ክፍል ላይ አለመገደቡና
- የጽንሰ ሃሳብ ግንዛቤ ሳያስጨብጥ  ተማሪዎችን በጭፍን ወደ ተግባቦት ልምምድ ውስጥ ማስገባቱ፣ ተጠቃሽ መሆናቸውን Batsone(1994) ላይ አስገነዝቧል፡፡

ለውጤት ተኮርና ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረቦች መካከል መሰረታዊ የሆኑ ልዩነቶች መኖራቸውን ከገለጻው መረዳት የቻላል፡፡ምክንያቱም የመጀመሪያው በቅርጽ ላይ ሲየተኩር  ሁለተኛው ደግሞ በአጠቃቀም ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በመቀጠልም የትምህርቱ አቀራረብም በቅርጽ ላይ ከሚደረግ የጽንሰ ሃሳብ ማስጨበጥ ልምምድ ተነስቶ በተገቢው ሁኔታ ወደ አውዳዊ የተግባቦት ልምምድ ሊሸጋገር እንደሚገባውና የተማሪዎችም ልምምድ በተወሰነ የቋንቋ ክፍል ወይም ቅርጽ ላይ መገደብ እንደሌለበት ይገልጻሉ፡፡

## 2.4. የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

በመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ግብ መቺ መሆን የሚችሉት አንዱ ሌላውን እያጠናከረ በሥረዓት ሲደራጁ ነው፡፡ በሥርዓት የተደራጀ የሰዋስው ትምህርት ልምድ ቀዳማዊ ለተከታዩ መሠረት በሚሆን መልኩ ሊዋቀር ስለሚቺል ውጤታማ  ትምህርት ለመግኘት ከማገዙ በተጨማሪ ተማሪው ቀድሞ ያልተገነዘበውን እንዲገነዘብ በመጀመሪያ ያገኘውን ትምህርት ተከትሎ የሚመጣውን ትምህርት ስለሚያዳብረው  እንዲያግዘው ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርትም ልምዶች ሲደራጁ ደግሞ ከቀላል ወደ ከባድ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ፣ከሚታወቅ ወደ ማይታወቅ እያደጉ እንዲዋቀሩ ያስፈልጋል ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ Tylor(1949፡84) የትምህርት ይዘትን ለማደራጀት በምንነሳበት ጊዜ በትምህርቶቹ መካከል የሚኖረውን የጊዜና የቦታ ግንኙነትን መመልከት እንዳለብን ይጠቁማል፡፡ ከዚህ አንጻር የትምህርት ይዘቶቹ ደረጃ በሁለት አይነት ሊታይ ይችላል ማለት ነው፡፡ ይህም አንደኛው በአንድ የትምህርት አይነት ውስጥ የሚኖረውን ግንኙነት የሚመለከት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በአንድ ደረጃ በተለያየ የትምህርት አይነቶች  መካከል የሚኖረው ዝምድና የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚህም ግንኙነቶች ተዋረዳዊ /ቀጥተኛ/ና ጎናዊ ግንኙነቶች ወይም የአደረጃጀት ስልቶች በመባል የሚታወቁ ናቸው፡፡

የዚህ የጥናት ትኩረት በአንድ የትምህርት አይነት የሚቀርብ የትምህርት ይዘት የሚመለከት በመሆኑ ጎናዊ አደረጃጀትን አይመለከትም፡፡ ምክንያቱም  ውህደት ቀደም ሲል እንደተገለጸው በአንድ የክፍል ደረጃ ውስጥ የሚሰጡ የተለያዩ የትምህርት አይነቶች መካከል ያለውን ተዛምዶ ስለሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑትን ተገቢነት ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት የአደረጃጀት ስልቶችን ለማየት እንሞክራልን፡፡

### 2.4.1. ተገቢነት

የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች ተገቢ ሆነው መቅረብ አለባቸው፡፡ ተገቢ ይሁኑ ሲባል የቀረቡትን ይዘቶች ከተማሪዎቹ የመገንዘብና የመስራት አቅም በላይ አስቸጋሪ መሆን የለባቸውም ፡፡ የመጀመሪያው ይዘት ወይም መልመጃ ለሁለተኛው መልመጃ በር የሚከፍትላቸው መሆን አለበት፡፡በትምህርቱ ውስጥ የሚቀርቡ የተለያዩ ሰዋስው ቅርጾችና ፍቺዎቻቸው እንዲሁም አጠቃቀማቸው የተማሪውን እድሜ፣የእውቀት ዳራ፣የክፍል ደረጃ፣ፍላጎትና ዝንባሌን መሰረት ያደረጉ መሆን እንዳለባቸው Harmer (1987፡18) አስረድተዋል፡፡

#### 2.4.2. ተከታታይነት

ተከታታይነት በአንድ የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡ ይዘቶች በሚቀጥለው ምዕራፎች እየተከታተለ መምጣቱን የሚያመለክት ነው፡፡ በይዘቶች መካከል ያለው ድግግሞሽ ተማሪዎቹ የተማሩትን ትምህርት የበለጠ እያጠናከሩ እንድሄዱ ይረዳቸዋል፡፡ ትምህርቱ ረዥም ጊዜና የማየቋረጥ ክትትል የሚያስፈልገው ጉዳይ እንደመሆኑ በውስን የትምህርት ይዘት የተፈለገውን ለውጥ ያመጡ ዘንድ ተደጋጋፊነት ያላቸው የትምህርት ልምዶች እየተደጋገሙ ደረጃ በደረጃ መቅረብ ይኖርባቸዋል ይላሉ (Tylor (1949፡84) ፡፡

### 2.4.3. ተለጣጣቂነት

Larsen-Freeman (1991) እና Tylor (1949) እንደ ገለጹት ተለጣጣቂነት ተዋረዳዊ የትምህርት ይዘቶች አደረጃጀትን የሚመለከት ነው፡፡ በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች በሚዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች ያላቸውን ተዋረዳዊ ዝምድናና ተደጋጋፊነት የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን ይዘቶች እርስበርሳቸው ተቆላልፈው በመሄድ የተማሪው የቋንቋ ደረጃ እያደገ በሄደ ቁጥር በመማሪያ መጻህፍት ውስጥ ያሉ ይዘቶችም ስፋትና ጥልቀት እያገኙ እንዲሄዱ የሚደረግበት አደረጃጀት ነው ይላሉ፡፡

## 2.5. የቋንቋ መርሀ ትምህርትና መማሪያ መጻህፍት

#### 2.5.1. የቋንቋ መርሀ ትምህርት

ይህ ጥናት ትኩረቱን በመማሪያ መጽሀፍ ላይ ያደረገ ቢሆንም ለተማሪው መጽሀፍ መነሻው መርሀ ትምህርቱ በመሆኑና ያላቸውን ተያያዥነት ለመመልከት ይረዳ ዘንድ ስለ መርሀ ትምህርት ምንነት ጥቂት እንመለከታለን፡፡

እንደ Cunningsworth (1995) እና Dubin and Olshtain(1986)፣ መርሀ ትምህርት ከስርዓተ ትምህርቱ የሚነሳና ጠበብ ባለ መልኩ በአንድ የክፍል ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች በአንድ የትምህርት አይነት ምን መማር እንዳለባቸው የሚያመለክት ሰነድ ሲሆን በውስጡም

የትምህርቱን ዓላማ፣ግብ መምታቱ፣ይዘት እና የይዘቱን አቀራረብ፣የትምህርቱን ጊዜና ዓላማውን የሚፈተሽበትን ግምገማ የያዘ ሰነድ ነው፡፡መርሀ ትምህርት የህብረተሰቡን የትምህርት ይዘቶችን መርጦ ለማደራጀት የሚያስችል እና በአጠቃላይ በክፍል ውስጥ የሚደረጉ የመማር ማስተማር ክንውኑን ለመምራት የሚያሰችል ሰነድነው:: Ur,P. (1996)፡፡

የቋንቋ መርሀ ትምህርት ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ የትኛውን እውቀት ፣ክህሎት እና እሴት መማር እንዳለባቸው እና እንደሌለባቸው ፣የታቀደው ትምህርት ውጤት ለማምጣት ምን ልምዶች ወይም ይዘቶች ሊታቀፉ እንደሚገባ የመማር ማስተማር ተግባር እንዴት እንደምተገበር እና እንደሚገመገም የምያመለክት ሰነድ ነው ይላል፡፡ Ur,P. (1996)፡፡አያይዞም የቋንቋ መርሀ ትምህርት የትምህርቱን አቅጣጫ ከመምራቱም ባሻገር በታላሚው ቋንቋ በራስ የመተማመን ብቃት የሌላቸው መምህራንን የማበረታታት ሚና እንዳለው ይገልጻል፡፡

### 2.5.2. የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ዓይነቶች

የቋንቋ መጻህፍት የቋንቋ መመሪያ ሀሳቦችን መነሻ አድርገው የሚዘጋጁና አላማቸው ቋንቋን ማስተማር ሆኖ አቀራረባቸው ግን የተለየ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ አንዳንዶቹ ለሰዋስው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ለተግባቦት ትኩረት የሚሰጡ ናቸው፡፡ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍት አይነቶችን አስመልክቶ ምሁራን የተለያዩ ስያሜዎችን ሲጠቀሙ ይታያል፡፡ለምሳሌ Grant(1987) የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትን ሰዋስው ተኮር እና ተግባቦት ተኮር በማለት በሁለት ይፈርጁዋቸዋል፡፡በሌላ በኩል Dawson (1984) ደግሞ የቋንቋ መማሪያ መጻህፍትን መዋቅራዊ፣ሁኔታዊና አገልግሎታዊ ብለው በሶስት ከፍሏቸዋል፡፡ እነዚህን በምሁራኑ የተሰጡ ስያሜዎች የተለያዩ ይሁኑ እንጂ ይዘውት የተነሱት ዓላማ አንጻር በተመሳሳይ ጽንስ ሃሳብ ዙሪያ የሚያጠነጥን በመሆኑ ያላቸውን የባህሪ አንድነት በመንተራስ እንደሚከተለው አካቶ ለማቅረብ ተሞክረዋል፡፡

### 2.5.2.1. ሰዋስው ተኮር የመማሪያ መጻህፍት

ሰዋስው ተኮር የመማሪያ መጻህፍት የመዋቅራዊ ስነ ልሳን ንድፈ ሃሳባዊ መሰረትነት ያለው ነው፡፡ በዚህ መማሪያ መጻህፍት አዘገጃጀት የቋንቋ ትምህርት ትኩረት የሚሰጠው ለቋንቋው ሰዋስዋዊ ስርዓት ነው፡፡ በቋንቋ ሰዋስዋዊ ትክክለኛነት ላይ ተመስርቶ ታላሚውን ቋንቋ ለማስተማር በሚያስችል መንገድ የሚዘጋጅ ነው፡፡ የመጽሀፉ አዘገጃጀት ከተግባቦት ይልቅ ስርዓት ላይ ያነጣጠረ እንደመሆኑ የትምህርቱን ዓላማ ለማስፈጸም የሚመረጡ ይዘቶች ከቋንቋ ሰዋስዋዊ ባህሪ አንጻር በቅደምተከተል የሚቀርቡበት ነው፡፡Grant, N. (1987)፡፡

### 2.5.2.2. ተግባቦት ተኮር የመማሪያ መጻህፍት

ተግባቦት ተኮር የመማሪያ መጽሀፍ የማህበራዊ ስነ ልሳን ንድፍ ሀሳባዊ መሰረትነት ያለው ነው፡፡ ይህ የመማሪያ መጽሀፍ የቋንቋው ለተግባቦት ትምህርት በሰዋሰው ላይ ከማተኮር ሂደት ተከትሎ መዘጋጀት እንዳለበት የሚያምን ሲሆን፤ በዚህ መጽሀፍ አቀራረብ በክፍል ውስጥ የሚተገበሩት መስተጋብር አማካኝነት የተግባቦት ብቃታቸውን እንዲያሳድጉ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ስለሆነም ከመጻፍና ከማንበብ ይልቅ ለማዳመጥና ለመናገር የበለጠ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል እናም ቀደም ስል የጠቀስናቸው የጽንሰ ሃሳብ ዝምድና አንጻር በተግባቦት ተኮር የመማሪያ መጻህፍት ስር የሚመደቡ ናቸው፡፡ Grant,N(1987)፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1. የምርምሩ ስልት

ይህ ጥናት ከምርምር ዘርፎች መካከል አይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን አቀራረቡ ደግሞ በገላጭ ስልት ነው፡፡በዚህ ዘዴም ጥናቱ በ7ኛ ና 8ኛ ክፍል የአማርኛ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ፍተሻ የሚገኘውን ውጤት መተንተን፡፡

## 3.2. የጥናቱ የመረጃ ምንጭ

የዚህ ጥናት መረጃ የተጠናከረው በሰነድ ፍተሻ ላይ ነው፡፡ በሰነድነት ያገለገሉትም ከላይ በተጠቀሰው በኦሮሚያ ክልል ኢአፈፊት ለሆኑ ተማሪዎች የተዘጋጀ የ7ኛና8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ናቸው፡፡

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

### 3.3.1. የሰነድ ፍተሻ

የዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ምንጮች በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋለው በኦሮሚያ ክልል በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፈ ፈት ለሆኑ ተማሪዎች የተዘጋጀ የ7ኛና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ነው፡፡ ግምገማው የሚካሄደው ክለሳ ድርሳን ውስጥ በቀረበው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ንድፈ ሃሳባዊ መሰረቶች ላይ ተመርኩዞ ሲሆን አጥኚዋ እነዚህን ንድፈ ሃሳቦች መሰረት በማድረግ በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት ትኩረት ሰጥታ ገምግማለች ፡፡ከዚህም በተጨማሪ መማሪያ

መጻህፍቱ ለደረጃው ከተዘጋጁት መርሀ ትምህርቶች ጋር ያላቸውን ዝምድና በሠነድ ፍተሻ ለማየት ተሞክረዋል፡፡

### 3.3.2. ቃለ መጠየቅ

በዚህ ጥናት የተካተቱት መፅሀፉን የሚያስተምሩ መምህራን ያላቸውን አስተያየት በቃለ መጠይቅ አማካኝነት በመሰብሰብ መረጃውን ለማጠናከር ተሞክረዋል፡፡እነዚህ መምህራን በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ስለስዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ያላቸውን አስተያየት ለማወቅ ቃለ መጠይቅ ተዘጋጅቷል፡፡ የቃለ መጠይቁ ጭብጥም በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አደረጃጀት ዙሪያ ነው፡፡

### 3.3.3 የጽሁፍ  መጠየቅ

በዚህ የ ጽሁፍ መጠየቅ  የተሳተፉት መጽሃፉን  የሚማሩት ተማሪዎች  ያላችውን አስታየት በጽሁፍ መጠየቅ አማካኝነት በ መሰብሰብ መረጃን ለማጠናከር ተሞክረዋል ፡፡

### 3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ

ይህ ጥናት አይነታዊ የምርምር *(Qaulitative research method*) ዘዴን በመጠቀም ከመጽሀፉ በሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡትን መረጃዎች በገላጭ (*Discriptive*) ስልት ቀርበዋል ፡፡ ግምገማው የተካሄደውም በክለሳ ድርሳን ላይ በቀረቡ ንድፈ ሐሳቦች አማካኝነት ነው፡፡ በዚህ ንድፈ ሐሳቦች መሠረትም በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ በተካተቱ በሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ ፍተሻ ተደርጎ ተተንትኗል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃዎች ትንተና የውጤት ማብራሪያ

## 4.1. የመረጃዎች ትንተና

የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት በኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ እና በነቀምቴ መምህራን ትምህርት ኮለጅ በትብብር ተዘገጅተው በኦሮሚያ ክልል እንዲስማሙ ተደርገው በ2014 ዓ.ም ተዘጋጅተው በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ የዋሉ ሲሆኑ መጻህፍቱ 120፣120 የገጽ ብዛት አሏቸው፡፡ የመማሪያ መጻህፍቱ የተዘገጁበት ዓላማ በየደረጃው የሚገኙ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ በብቃት ማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብና መጻፍ ክሂሎችን እንዲሁም ቃላት፣ የስነጽሁፍና የሰዋስው እውቀትን ለማዳበር እንዲችሉ ለማድረግ እነደሆነ በመግቢያው ላይ ተጠቅሷል፡፡

ተተኳሪው መማሪያ መጻህፍት አስር፣አስር ምዕራፎችያሏቸው ሲሆኑ በእያንዳንዱ ምዕራፍ ከትምህርት አንድ እስከ ትምህርት ሰባት በተለያዩ ይዘቶች የተከፋፈሉ ሲሆን በስራቸውም መልመጃዎችን አካተው ይዘዋል፡፡በእነዚህ መጻህፍት ውስጥ በትምህርትነት ከተያዙት ይዘቶች መካከል አንዱ ሰዋስው ይዘት ነው፡፡

ኢ-አፈ-ፈት ለሆኑ ተማሪዎች የተዘጋጀ የአማርኛ ቋንቋ አጠቃላይ ቅኝት በአጠቃላይ በኦሮሚያ ክልል የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋመማሪያ መፃህፍት ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ ይዘቶች መካከል የተወሰኑት ስዋስው ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ይህንን በሚቀጥለው ሰንጠለዥመመልከት ይቻላል፡፡

ሰንጠረዥ፡ 1፡ የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ አጠቃላይ ቅኝት

| ተ.ቁ. | ምዕራፍ | የምዕራፎቹ ዋና ዋና ርዕሶች | የምንባቦቹ ንዑስ ርዕሶች | የምንባቡ ዓይነት | የቀረበው መልመጃ ብዛት | የቀረበው የሰዋስው መልመጃ ብዛት | የቀረበው የሰዋስው ገለጻ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አንድ | እሬቻ | የእሬቻ በዓል | ኢ-ልቦለድ | 5 | 1 | 1 |
| 2 | ሁለት | መልከዓ ምድር | ቅንጭብጭብ ዕሁፎች | ኢ-ልቦለድ | 5 | 1 | 1 |
| 3 | ሦስት | የትራፊክ ደህንነት | በትራፊክ አደጋ የተሰናከለው ጀግና | ኢ-ልቦለድ | 5 | 1 | 1 |
| 4 | አራት | የሕይወት ታሪክ | ፕሮፌሰር ገቢሳ ኤጀታ ማን ነው? | ኢ-ልቦለድ | 6 | 1 | - |
| 5 | አምስት | ሱሰኝነት | የጫት ሱስ | ኢ-ልቦለድ | 6 | 1 | 1 |
| 6 | ስድስት | ግብር | ግብር መክፈል ለሀገር እድገት | ኢ-ልቦለድ | 6 | 1 | 1 |
| 7 | ሰባት | ታዋቂዋ ሴት | የመጀመሪያዋ ጥቁር አፍርካዊት የወርቅ ሜዳሊስት | ኢልቦለድ | 6 | 1 | 1 |
| 8 | ስምንት | ኤች አይ ቪ/ ኤድስ | አጫጭር ግጥሞች | ልቦለድ | 7 | 1 | 1 |
| 9 | ዘጠኝ | ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር | ቅንጫቢ ታሪክ | ልቦለድ | 5 | 1 | 1 |
| 10 | አስር | ተረት | ተረት (አጫጭር አንቀጾች | ልቦለድ | 7 | 1 | 1 |
| | | | | ድምር | 58 | 11 | 9 |

**ሰንጠረዥ፡2፡ የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ አጠቃላይ ቅኝት**

| ተ.ቁ. | ምዕራፍ | የምዕራፎቹ ዋና ዋና ርዕሶች | የምንባቦቹ ንዑሳን ርዕሶች | የምንባቡ ዓይነት | የቀረበው መልመጃ ብዛት | የቀረበው የሰዋስው መልመጃ ብዛት | የቀረበው የሰዋስው ገለጻ ብዛት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አንድ | ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት | ሰርጉማ | ኢ-ልቦለድ | 6 | 1 | - |
| 2 | ሁለት | ስርዓተ ፆታ | ስርዓተ ፆታዊ አድልዎ | ኢ-ልቦለድ | 4 | 1 | 1 |
| 3 | ሦስት | የመረጃ ትስስር ቋት | ማህበራዊ መገናኛ | ኢ-ልቦለድ | 5 | 1 | 1 |
| 4 | አራት | ተላላፊ በሽታዎች | ኤች አይ ቪ/ ኤድስ የሚያስከትላው ቀውሶች | ኢ-ልቦለድ | 4 | 1 | - |
| 5 | አምስት | አርበኝነት | የአርበኝነት መገለጫዎቹ | ኢ-ልቦለድ | 4 | 1 | 1 |
| 6 | ስድስት | ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር | ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር እና ሰቆቃዎቹ | ኢ-ልቦለድ | 4 | 1 | - |
| 7 | ሰባት | የበጎ ፍቃድ አገልግሎት | ለወገን ደራሿ ነርስ | ኢ-ልቦለድ | 4 | 1 | - |
| 8 | ስምንት | ባህላዊ ቅርሶች | የገዳ ሥርዓት | ኢ-ልቦለድ | 4 | 1 | 1 |
| 9 | ዘጠኝ | የቋንቋ አገልግሎት | የቋንቋ አገልግሎት | ኢ-ልቦለድ | 4 | 1 | 1 |
| 10 | አስር | የስራ ስነ ምግባር | የስራ ቸልተኝነትና መዘዙ | ኢ-ልቦለድ | 4 | 1 | - |
| | ድምር | | | | 43 | 10 | 5 |

## 4.2. በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ

### 4.2.1. ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ

ከላይ በክለሳ ድርሳን ላይ እንደተጠቀመው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብ ስልት ተማሪዎች በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የቀረበውን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በምሳሌዎች እየታገዙ መልመጃዎችንና ትግበራን ከሰሩ በኋላ በሂደት የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓትን በራሳቸው ጥረት እንድደርሱበት የሚያደርግ አቀራረብ ነው፡፡

Cunningsworth (1995፡99) እና woods (1995፡76) እንደገለፁት ለትምህርት በቀረበው ሰዋስዋዊ ቅርፅ ዙሪያ የተለያዩ ምሳሌዎችን በማቅረብ በምሳሌዎቹ መሠረት ተማሪዎች የተለያዩ መልመጃዎችን ከሰሩ በኋላ ህጉን በራሳቸው ጥረት እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው። ይህ መልመጃም በመጀመሪያ ምሳሌዎች ከቀረቡ በኋላ በምሳሌውቹ መሰረት እንዲሰሩ የሚያደርጉ ናቸው።ለዚህም እነደ ማሳያ በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ ምሳሌዎችን ጠቅሰው የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች መካከል ቀጥሎ የቀረበው ይገኝበታል፡

**ትምህርት ስድስት፡ ስዋስው**

***መልመጃ ስድስት***

*ምሳሌውን መሠረት አድርጋችሁ ቀጥሎ የቀረቡትን የቁጥር ስህተት ያለባቸውን ዓረፍተነገሮች በማስተካከል ደግማችሁ ፃፉ።*

*ምሳሌ፡- እያንዳነዱ ሰው መናገር አለባቸው።*

*ሲስተካከል፡ እያንዳንዱ ሰው መናገር አለበት።*

- *አንቺ ከትምህርት ቤት ትመጣላችሁ።*
- *ነጋዴው ሸቀጦቹን ሸጠው። /ገፅ፡ 44/*

*ከላይ የቀረበው ይዘት ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የቀረበ ቢሆንም በምሳሌው ብቻ በመታገዝ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ሥርዓት ማወቅ ለተማሪዎቹ ቀላል አይሆንም፡ እንድሁም በ8ኛ ክፍል መጽሀፍ ምዕራፍ አንድ ትምህርት ስድሰት*

*መልመጃ አምስት*

*የሚከተሉትን ዓረፍተነገሮች ሰዋስዋዊ ሥርዓቱን ጠብቃችሁ አስተካክላችሁ ፃፉ።*

*ምሳሌ፡- ወጡ ተራራውን በምርኩዝ እየተደገፉ አዛውንቱ።*

*የተስተካከለ ፡ አዛውንቱ በምርኩዝ እየተደገፉ ተራራውን ወጡ።*

- *ጠንካራ እንደ አንበሳ ነው።*
- *ጎበዝ እሷ ናት ተማሪ። /ገፅ ፡ 14/*

ይህን የቀረበውን ምሳሌ ስንመለከት ተማሪዎች የተሰጣቸውን ምሳሌ በመከተል በራሳቸው እንዲሰሩ የሚያደርግ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ምሳሌውን ተንተርሰው እንዲሰሩ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ ትምህርት ሰዋሰዋዊ አገባባቸው ያልተስተካከሉ ዓረፍተ ነገሮችን አስተካክለው እነዲፅፉ የሚረዳቸው ይዘት ነው፡፡ ነገር ግን በቀደመው የትምህርት ይዘት ውስጥ ስለ ሰዋስዋዊ አገባብ ህግ አላስቀመጠም ፡፡ ይህ ደግሞ ካላቸው የቋንቋችሎታ ጋር ሲነጻጸር የቀረበው ይዘት ሊከብዳቸው ይችላል፡፡ ምክንያቱም አማርኛን እነደ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሚማሩ ተማሪዎች በአብዛኛው ቋንቋውን የሚጠቀሙት በትምህርት ክፍለ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም አማርኛቋንቋን መማር የጀመሩት ከአምስተኛ ክፍል ሲሆን በሰባተኛና ስምንተኛ ክፍል ውስጥ ሰዋስዋዊ አገባባቸው ያልተስተካከሉ ዓረፍተነገሮችን አስተካክሎ መጻፍ ካላቸው ቅድመ እውቀትና የትምህርት ልምድ አንፃር የተማሪውን አቅም ያገናዘበ አይደለም፡፡ በእርግጥ ይዘቱ በመርሀ ትምህርቱ ላይ ተንተርሶ የቀረበ ቢሆንም በቀደመው የሰዋስው ይዘት አገባባዊስህተት ማስተካከል ለማወቅ የሚረዱ ልምምዶች አልተቀመጡም፡፡

## ትምህርት ስድስት ፡ ሰዋስው

*መልመጃ አራት*

*ሀ.* ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት ውስጥ ተውሳከ ግሶችንና መስተዋድዶችን ለይታችሁ ጻፉ፡፡

ምሳሌ፡ ቶሎ - ተውሳከ ግስ

ከ - መስተዋድድ

- ጠዋት
- ወደ
- ላይ
- በፍጥነት
- ክፉኛ

ለ. በሚከተሉት አረፈተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ተውሳከ ግስ ወይም መስተዋድድ መሆናቸውን ለይታችሁ በቃል ምልሱ፡፡

ምሳሌ፡- አስቴር ትምህርት ቤት አርፍዳ ሄደች፡፡ ተውሳከ ግስ፡፡

ልጁ አሁን ይመጣል

ለሊሴ ወደ ባቱ ሄደች

ገጽ/87/

ከላይ የተጠቀሱት መልመጃዎች ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ አቀራረብን የተከተሉ ቢሆንም በዚሁ መጽሀፍ ውስጥ /ገፅ 63/ የቃል ክፍሎች የሚል ማስታወሻ ሰጥቶ /ገጽ 87/ ላይ ምሳሌዎች በመስጠት እንዲሰሩ ማድረጉ ለተማሪዎቹ ቀድሞ የተማሩትን ወደኃላ ተመልሰው እንዲያስታውሱና በመርሀ ትምህርቱ የተጠቀሙ ይዘቶች በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ መገኘታቸው ከጠንካራ ጎን ይጠቀሳሉ፡፡

### 4.2.2. ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ

ይህ አቀራረብ በመጀመሪያ በትምህርት በቀረበው ስዋስዋዊ ይዘት ላይ ጥቅል የሆነ ማብራሪያ ካቀረበ በኃላ በምሳሌ በማሳየት ከዚህ ተነስተው ተማሪዎች መልመጃዎችን እንዲሰሩና ህጉን፣ እንዲያውቁ የሚያደርግ ሂደት በመሆኑም መመሪያን ፣ፅንስ ሀሳብን እና ንድፈ ሀሳብን በመግለጽ ወይም በመተንተን ለማስተማር የሚሞክር አቀራረብ ነው፡፡ በአቀራረቡም የቋንቋን ህግ በቅድሚያ ነግሮ ምሳሌ በመስጠት ሌሎች ተመሳሳይ ስራዎችን መስራት ይመለከታል፡፡ መልመጃዎቹም በቃልና በጽሁፍ የሚመለሱ ይሆናሉ፡፡

በኦሮሚያ ክልል ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ በጽሀፍ ላይ በተደረገው የሰነድ ፍተሻ 7ኛ ክፍል ስምንት ፣ በስምንተኛ ክፍል አምስት ያህል የሚሆኑት

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ማብራሪያ የተሰጣቸው ሲሆን በመጽሀፉ ውስጥ ገለፃ ወይም ማብራሪያ የተሰጣቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ስለ ስሞች፣ተፅኦ፣የወልና የረቂቅ ነገሮች መጠሪያ ቃላት ስለ ግስ ምንነትና ተግባር ገጽ/10ና 11/ ቅድመና ድህረ ግንድ ቅጥያ ገጽ/21/፣ ስለ ባለቤት፣ተሳቢና ግስ ገጽ/66/፣ስማዊ ሀረግና ግሳዊ ሀረግ ገጽ/90/፣አያያዥ ቃላት ገጽ/102/ እና 103 በሰባተኛ ክፍል ላይ የቀረበ ማብራሪያ ሲሆን የዓረፍተ ነገር መዋቀር ገጽ/26ና 27/፣ ጥገኛ ምዕላድና ነፃ ምዕላዶችን መለየት ገጽ/38/፣የቃል ክፍሎች ገጽ/63/፣ድርብ ዓረፍተ ነገሮች መመስረት ገጽ/77 እና ሰዋስዋዊ አገባባቸው የተዛቡ ዓረፍተ ነገሮችን ማስተካከል ገጽ/106/ ስምንተኛ ክፍል መጽሀፍ ላይ አጫጭር ገለፃዎች ወይም ማብራሪያዎች ተሰጥተዋል፡፡

ይህ የስዋስው ይዘቶች ከጥቅል ወደ ዝርዝር ባህሪያቸው መቅረባቸውን ያሳያሉ፡፡ እንደምሳሌነት የተወሰኑትን እንመልከት፡፡

ቅድመና ድህረ ግንድ ቅጥያ/ገጽ፡11/

ቅድመ ግንድ ቅጥያዎች ከቃሉ በስተመጨረሻ የሚቀጠሉ ሲሆኑ ድህረ ግንድ ቅጥያዎች ከቃሉ በስተመጨሻ የሚቀጠሉ ናቸው፡፡

ለምሳሌ፡- በተማሪዎች፣

- በ- ቅድመ ግንድ ቅጥያ፣
- ተማሪ- ግንድ ፣
- ዎች- ድህረ ግንድ ቅጥያ

በምሳሌው መሠረት ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት ላይ ቅድመ ግንድና ድህረ ግንድ ቅጥያዎችን ለይታችሁ ፃፉ፡፡

**ሠንጠረዥ-3፡ ቅድመና ድህረ ግንድ ቅጥያን መለየት**

| ተ.ቁ. | ቃል | ቅድመ ግንድ ቅጥያ | ድህረ ግንድ ቅጥያ |
|---|---|---|---|
| 1 | ስለቤታችን | ስለ- | -ኣችን |
| 2 | የቆሻሻው | የ- | -ው |

**ስምና ግስ ገላጭ**

ስም የምንላቸው ቃላት የነገሮች መጠሪያ እንደሆኑ በምዕራፍ አንድ ትምህርታችሁ ተምራችኃል፡፡ የስም ገላጭ ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ ከስም ቀድመው በመግባት የስሙን ባሕሪ፣ቅርፅ፣መጠን፣ቀለም ,፣ ሁኔታ ወዘተ የሚገልፁ ናቸው፡፡

ምሳሌ፡-

- ባህሪ፡ ደግ፣ክፉ
- መጠን፡ ትልቅ፣ትንሽ
- ቀለም፡ ነጭ፣ጥቁር
- ቅርፅ፡ ክብ፣ዝርግ
- ሁኔታ፡ አዲስ፣አሮጌ

1. ቀጥሎ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ስም ወይም የስም ገላጭ በማለት መድቡ፡፡

ምሳሌ፡ ሀ. <u>አስተዋይዋ</u> ሀሊማ መጣች ፡፡

- አስተዋይዋ - የስም ገላጭ
- ሀሊማ - ስም

ለ. አየለ <u>ከፍተኛ</u> <u>ውጤት</u> አስመዘገበ፡፡

- ከፍተኛ- የስም ገላጭ
- ውጤት- ስም

ሐ. <u>ብዙ</u> <u>ሰዎች</u> ለስራ ያላቸው አመለካከት ጥሩ አይደለም፡፡

- ብዙ- የስም ገላጭ
- ሰዎች - ስም

መ. ደራሲው <u>ጥሩ</u> <u>መፅሀፍ</u> ፃፈ፡፡

- ጥሩ- የስም ገላጭ
- መፅሀፍ- ስም

2. ምሳሌውን መሠረት አድርጋችሁ በሰንጠረዥ ውስጥ በቀረቡት ዓረፍተነገሮች ውስጥ ስም እና የስም ገላጭ የሆኑ ቃላትን ፃፉ፡፡

**ሠንጠረዥ-4፡ ስምና የስም ገላጭቃላትን መለየት**

| ተ.ቁ. | ዓረፍተነገር | ስም | የስም ገላጭ |
|---|---|---|---|
| 1 | በርካታ ሰዎች መጡ | ሰዎች | በርካታ |
| 2 | ወንድሜ ትልቅ ቤት ገዛ | | |
| 3 | ጎበዙ መምህር መጣ | | |

በ8ኛ ክፍል መመሪያ መፅሀፍ ውስጥ ደግሞ በገፅ /26 ና 27/ የዓረፍተነገር መዋቅር /ገፅ 38/፤ ጥገኛናነፃ ምዕላዶች /ገጽ 63/፤የቃል ክፍሎች /ገፅ 97/ ድርብ ዓረፍተ ነገሮች /ገጽ 106/ ፤ የዓረፍተ ነገር አወቃቀርሥርዓት ቀርበዋል፡፡እነዚህ መልመጃዎችና አጫጭርማብራሪያዎች የስዋስው ትምህርት ይዘቶች ከጥቅል ስዋስዋዊ ባህሪያቸው ወደ ዝርዝር ባህሪያቸው መቅረባቸውን ያሳያል፤ ከነዚህም ለማሳያነት፡-

የቃል ክፍል ቃላትን ለማጥናት የሚደረግ ክፍፍል ነው፡፡

ስም፡- የሚከተሉትን የቅርፅና የአገባብ ባህሪያት አሉት፡፡

- ጠቋሚ ወይም መጣኝ መስተዓምርን ቀድመው ሊገቡ ይችላሉ፡፡

መስተዓምር ፡- የሚባሉት ቃላት አንድነገር ድርጊትና ባህሪ ከሌላ ነገር ድርጊትና ባህሪ ተለይቶ የታወቀ መሆኑን ወይም አለመሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ መስተዓምር ማለትም የሚያሳውቅ የሚለይ እንደ ማለት ነው፡፡ ስያሜውን የሚያሳውቀው በሶስት ምንገድ ነው፡፡አንደኛው ከሌሎች ነገሮች ለይቶከሚገኝበት ቦታ ወይም ጊዜ አንፃር በመጠቆም ነው፡፡ ሁለተኛው ነገሩ የማን እንደሆነ ለማገናዘብ ሲሆን ሦስተኛው ነገሩ በመጠን ሲተመን ምን ያህል እነደሆነ በመግለፅ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ያ፣ እነዚያ፣ይህ፣ እሱ፣እነሱ ወዘተ (ጌታሁን አማረ፡ 1990) እና (ባየ ይማም፡ 2006)፡፡

በአጠቃላይ በተደረገው የሰነድ ፍተሻ በተተኳሪው መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ ለናሙናነት ከተጠቀሱት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረበው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በተለያዩ ዘርፎች ይገኛሉ፡፡ይሁን እንጂ ተማሪዎቹ የቀረቡላቸውን ማስታወሻዎች ተከትለው በመሄድ ሁሉንም ላይረዱት ይችላሉ፡፡ በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ማስታወሻዎችና መልመጃዎች ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ስልትን ተከትለው የቀረቡ ይሁኑ እንጂ ማስታወሻውን ብቻ መሠረት አድረገው የሚሰሩት ተመጣጣኝ የሆነውን የመስተዓምር ትምህርት ለማወቅ ሊቸግራቸው ይችላል፡፡ምክንያቱም በዚሁ በ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ /ገጽ 63/ የቃል ክፍል ውስጥ የተገለፁት የመስተዓምር አይነቶችና መስተዓምር በሚል ማስታወሻ የተገለፀው በኦሮሚያ ክልል ኢ-አፈ-ፊት ለሆኑ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚከብድ ስለሚሆን በምንጩ ላይ እንደተገለፀው መስተዓምሮችን ጠቋሚ፣አገናዛቢና መጣኝ ተብለው የሚከፈሉ መሆናቸውን በዝርዝር ያስቀምጣል፡፡በዚህ መልክ ተተንትኖ ቢቀርብላቸው የበለጠ አንብበው ለመረዳት አያስቸግራቸውም፡፡

በአጠቃላይ ኢ-አፈ-ፈት ለሆኑ ተማሪዎች የቋንቋውን ህግ ከማብራሪያው ወይም ከማስታወሻው ተረድተው እንድለማመዱ ስለሚያደርግ አቀራረቡ ለተማሪዎች ምቹ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን በመፃህፍቱ ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የቀረቡ ይዘቶች ጥቂት በመሆናቸው ውስንነት ይታይባቸዋል፡፡

### 4.2.3. ውጤት ተኮር አቀራረብ

በክለሳ ድርሳኑ ላይ እንደተጠቀሰው ውጤት ተኮር አቀራረብ ስልት ተማሪዎች በቀረበው ዝርዝር ህግ ላይ ተመስርተው ትክክለኛ የሆነ መልስ አንዲሰጡ ይፈለጋል ፡፡ ይህ ማለት በመጀመሪያ የሚቀርበውን ስዋስዋዊ ይዘት አስመልክቶ የቋንቋው ሥርዓት የሚፈቀደውን ወይም የሚከተለውን ህግ መነሻ ያደረገ ማብራሪያ ትንታኔ በመስጠት ተማሪዎች ህጉን መነሻ በማድረግ የሚቀርቡላቸውን መልመጃዎች እንዲሠሩ የሚያስችል አቀራረብ ነው፡፡

የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መካከል በተለያዩ አውዶች አማካኝነት የቋንቋውን ቅርፅ ከተግባቦት አገልግሎት ጋር በማስተሳሰር ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስችል አቀራረብ የተከተለ ነው፡፡ የተወሰኑትን ለአብነት እናያለን፡፡ የ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ /ገጽ 21/ በምሳሌው መሰረት ቀጥሎ ከቀረቡላቸው ላይ ቅድመና ድህረ ግንድ ቅጥያዎችን ለይታቸሁ ፃፉ፡፡

በቋንቋው ሰዋስዋዊ ሥርዓት ላይ ተመስርተው በቃላት ላይ የተጨመሩ ቅጥያዎችን ለይተው ይጽፋሉ፡፡ በተጨማሪም /ገፅ 32/ ምሳሌውን መሠረት አድረጋችሁ በሰንጠረዥ ውስጥ በቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ስምና የስም ገላጭ የሆኑ ቃላትን ፃፉ፡፡

**ሠንጠረዥ-5፡ ስምና የስም ገላጭ የሆኑትን መለየት**

| ተ.ቁ. | ዓረፍተ ነገር | ስም | የስም ገላጭ |
|---|---|---|---|
| 1 | ወንድሜ ትልቅ ቤት ገዛ | | |
| 2 | ጎበዙ መምህር መጣ | | |

ስርዓቱን ጠብቀው ከዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ስምና የስም ገላጮችን ለይተው እንዲፅፉ የሚያደርግ ነው፡፡በተተኳሪው መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በቋንቋው ሰዋስዋዊ ስርዓት ላይ ማነጣጠሩ ውጤት ተኮር አቀራረብን የተከተሉ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ይህ ማለት ከሂደት ተኮር ይልቅ የበለጠ ድርሻ የሚይዙት ውጤት ተኮር በሆኑ ስልቶች የቀረቡ የሰዋስው ትምህርቶች ናቸው ማለት ነው፡፡

8ኛ ክፍልን ስንመለከት በተመሳሳይ በተተኳሪው መፅሀፍ ውስጥ ውጤት ተኮር ሆነው የተካተቱት የትምህርት ይዘቶች መካከል /ገጽ 14/ የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮች ሰዋስዋዊ ስርዓትን ጠብቻሁ አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡

1. ጠንካራ እንደ አንበሳ ነው፡፡
2. ጎበዝ እሷ ናት ተማሪ ፡፡

/ገፅ 51/ ቀጥሎ የቀረቡላችሁን ድምፆች በማቀናጀት ትረጉም አዘል ቃላት መስርቱ፡፡ በመሰረታችሁት ቃላትም ዓረፍተ ነገር ስሩ፡፡ ጨ፣ሰ፣ደ፣የ፣ቀ፣ን፣መ፣ረ፣ጠ፣ፈ፣ታ፣ወ፣በ፣ለ፡፡

ምሳሌ፡- በ- **በላ**፡፡

- ልጁ የጓደኛውን ገንዘብ **በላ**፡፡

መልመጃዎቹ በቋንቋው ሰዋስዋዊ ሥርዓት ላይ ማነጣጠራቸው ውጤት ተኮር አቀራረብን የተከተሉ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ሌሎች መልመጃዎችንም ስናይ ከሂደት ተኮር ይልቅ የበለጠ

ድርሻ የሚይዙት ውጤት ተኮር በሆነ ስልት የቀረቡ የሰዋስው ትምህርቶች ናቸው። በትክክል ሰዋስዋዊ ህጉን መተግበር ላይ ያነጣጠሩ በመሆናቸው ውጤት ላይ ትኩረት አድርገው የቀረቡ ናቸው ለማለት ያስችላል። መርሀ ትምህርቱም በውጤት ተኮር ስልት የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች በማስተዋል የሚሰሩ መሆናቸውን ይጠቁማል።

### 4.2.4. ሂደት ተኮር አቀራረብ

ሂደት ተኮር አቀራረብ ስልት ተማሪዎች በቋንቋው ይበልጥ እነዲጎለብቱና ተግባቦታዊ በሆነ ስልት የቋንቋውን ቅርፆች በይበልጥ እንዲጠቀሙባቸው የሚያስችል የአቀራረብ ስልት እንደ ሆነ በክለሳ ድርሳኑ ላይ ተጠቁመዋል። የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፅሀፍ ካካተታቸው ይዘቶች መካከል ሂደት ተኮር በሆነ ዘዴ የቀረበው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ጥቂት ቢሆኑም ቀጥሎ የቀረቡትን መመልከት ይቻላል።

1. /ገፅ 55/ ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት፣

የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ከቀረቡት አያያዥ ቃላት በመምረጥ አያይዛችሁ ድርብ ዓረፍተነገሮችን መስርቱ።

- እንጂ
- ይሁን እንጂ
- ስለዚህ
- ስለመሆኑም

ምሳሌ፡- ማጥናት እፈልጋለሁ።

- ፀጥታ መኖር አለበት።
- ማጥነት እፈልጋለሁ ፤ ስለዚህ ፀጥታ መኖር አለበት።

2. /ገፅ 103/ ትክክለኛውን አያያዥ ቃል በመጠቀም ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን ወደ ድርብ ዓረፍተ ነገሮች ቀይሯቸው።

ሠንጠረዥ-6፡ አያያዥ ቃላት በመጠቀም ነጠላ ዐረፍተነገሮችን ወደ ድርብ ዐረፍነገሮች መቀየር

| ተ.ቁ. | ዓረፍተነገር | አያያዥ ቃል | ዓረፍተነገር |
|---|---|---|---|
| 1 | ሰማዩ ጠቁሯል | እና<br>ወይም<br>ነገርግን<br>ስለዚህ<br>እንዲሁም | መዝነቡ አይቀርም |
| 2 | በሱስ ተጠምደ፡፡ | | ጤናው ታወከ |
| 3 | ልጁ ታመመ፡፡ | | ወደ ሀኪም ቤት አልሄደም |
| 4 | ልጁ ክፉኛ ወደቀ፡፡ | | ምንም አላለቀሰም |
| 5 | አባቷ ይወዳታል፡፡ | | ያስብላታል |
| 6 | ችግኞቹ ውሀ አላገኙም፡፡ | | አልጠወለጉም |

መልመጃዎቹ በሂደት ተኮር አቀራረብ የቀረቡና ጥሩ በሚባል አቀራረብ የቀረቡ ናቸው፡፡

የ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍን በሚመለከት /ገፅ 38/ ቀጥሎ ከቀረቡት ቃላት ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን ለይታችሁ አሳዩ፡፡

1. ወንበር 2. ወንድሞቻችን

የራሳችሁን አምስት አምስት ቃላት በመፈለግ ቃላቱ የያዙትን ነፃና ጥገኛ ምዕላዶችን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡

/ገፅ 98/ የሚከተሉትን ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን በማጣመር ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

1. ሀ. ደመናው ደመነ ፡፡ 2. ሀ. ከድጃ ገበያ ሄዳለች ፡፡

ለ. ዝናብ አልዘነበም፡፡ ለ. ክፍል ውስጥ አልገባችም፡፡

በተተኳሪው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መፃህፍት ውስጥ በሂደት ተኮር አቀራረብ የቀረቡት ይዘቶች ጥሩ ቢሆኑም ተማሪዎቹ ኢ-አፈ-ፊት ከመሆናቸው አንፃር ሲታይ በዚህ ሂደት የቀረቡት ይዘቶች ጥቂት ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ከመርሀ ትምህርቱ ጋር ሲታይ ግን ተመጣጣኝ የሆኑ ይዘቶች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በኦሮሚያ ክልል ኢ- አፈ-ፈት ለሆኑ ተማሪዎች በተዘጋጀው የሰባተኛና የስምንተኛ ክፍል መማሪያ መጻህፍት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብን ስንመለከት ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ይልቅ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ ለማቅረብ የተሞከሩ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የሚያመዝኑ ሲሆኑ ከውጤት ተኮርና ሂደት ተኮር የአቀራረብ ዘዴ አንፃር ደግሞ ከሂደት ተኮር ይልቅ ውጤት ተኮር በሆኑ ስልቶች የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች ተግባቦት ላይ ያተኮሩ ጥቂት መሆናቸው በጥናቱ ተረጋግጧል ። በመሆኑም ይዘቶቹ የተማሪዎቹን አፍልቆትና ተግባቦትን የሚያበረታቱ አይደሉም።

## 4.3. በመማሪያ መፃህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አደረጃጀት

### 4.3.1. ተገቢነት

Harmer (1987፡ 18) እንደሚያስረዱት በትምህርቱ ውስጥ የሚቀርቡት ቅርፆችና ፍቻቸው እንዲሁም አጠቃቀማቸው የተማሪውን እድሜ፣የእውቀት ዳራ፣የክፍል ደረጃ፣ ፍላጎትትንና ዝንባሌን መሠረት ያደረጉ መሆን እንደሚገባቸው ይገልፃሉ። የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ተገቢ ሆነው መቅረብ አለባቸው ሲባል የቀረቡት ይዘቶች ከተማሪዎቹ የመገንዘብና የመስራት አቅም በላይ አስቸጋሪ መሆን የለባቸውም ለማለት ነው። የመጀመሪያው ይዘት ወይም መልመጃ ለሁለተኛው መልመጃ በር የሚከፍትላቸው መሆን አለበት። ከላይ የቀረበውን ሀሳብ መሰረት በማድረግ በኦሮሚያ ክልል የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ የተማሪ መፃህፍት ከተገቢነት አኳያ የተደረሰበት መደምደሚያ እንደሚከተለው ቀርቧል።

የ7ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ /ገፅ 62/ ከዚህ በታች በተሰጡት ቃላት ባለቤትና ተሳቢ በማድረግ በምሳሌው መሠረት ዓረፍተ ነገር መስርቱ።

ምሳሌ፡- በሬ

- ባለቤት - በሬ የቤት እንስሳ ነው፡፡
- ተሳቢ - ከበደ በሬ ገዛ፡፡

/ገፅ ፡ 79/ መልመጃ አምስት በሚከተለው ፅሁፍ ውስጥ ያሉትን የተፀውዖ ስም፣ የወል ስምና የነገር ስም አውጡ፡፡

ከእነዚህ ምሳሌዎች የሰዋስው ይዘቶቹ የተማሪውን የእውቀት ዳራ እንዲሁም የክፍል ደረጃ ያላገናዘበ መሆኑን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የ8ኛ ክፍል መማሪያ መፅሀፍ ላይ እንዲሁ /ገፅ ፡ 52/ መልመጃ አራት (ለ) ከሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች በለቤትና ማሠሪያ አንቀጽ ለዩ ከማሠሪያ አንቀፅ ደግሞ ተሳቢና ግሱን ለዩ፡፡

ምሳሌ፡- ልጁ ቤት ገዛ፡፡ በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ ‹‹ልጁ›› ባለቤት››፣ ቤት ገዛ ‹‹ማሠሪያ አንቀጽ ፣ ‹‹ቤት›› ተሳቢ ፣ ‹‹ገዛ›› ደግሞ ግስ ነው፡፡

/ገፅ ፡ 76 /የራሳችሁን አምስት አምስት አረፍተ ነገሮች መስርቱና ተዋቃሪዎቹን ለይታችሁ አመልክቱ፡፡ /ገጽ ፡ 77/ የራሳችሁን አምስት አምስት ቃላት በመጠቀም ምዕላዶቹን ለይታችሁ አገልግሎታቸውን በቃል ተናገሩ፡፡

በአጠቃላይ የቀረቡ የሰዋስው ይዘቶች በአንድ ጥያቄ ውስጥ ሁለት ሦስት የሰዋስው ጥያቄዎች እንዲሰሩ ማድረግ በአመዛኙ ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ በመሆኑ ለ7ኛና 8ኛ ክፍል ኢ- አፌ-ፌት ተማሪዎች ታስቦ መቅረቡ የተገቢነትን ድክመቱን ያሳያል፡፡

### 4.3.2. ተከታታይነት

ተከታታይነት ሲባል በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረበ የስዋስው ትምህርት በየምዕራፎቹ መገኘቱን የሚመለከት ሲሆን በሌለኛው ደግሞ በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረበ የስዋስው ይዘት በቀጣይ የክፍል ደረጃ መምጣቱን የሚያመለክት ነው፡፡

በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረበ የሰዋስው ትምህርት በየምዕራፎቹ መገኘቱን በተመለከተ የ7ኛ ክፍል መጽሀፍ /ገጽ፡ 10) ስሞች የተፀውዖ፣የወል፣የረቂቅ ነገሮች መጠሪያ ቃላት ናቸው፡፡

- የተፀውዖ ስም፡ ሲፈን ፣አህመድ
- የረቂቅ ስም ፡ አየር፣እውቀት
- የወል ስም፡ ድመት፣ቤት

/ገጽ፡ 78/ ከዚህ በታች ያሉትን ቃላት በየስም አይነታቸው መድቧቸው፡፡

ምሳሌ፡- የተፀዖ ስም ፡ ኬናኦል

- የወል ስም ፡ ደብተር
- የነገር ስም ፡ አየር

/ገፅ ፡55/ በምሳሌው መሠረት ከዚህ በታች ጥንድ ጥንድ ሆነው የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ከቀረቡት አያያዥ ቃላት በመምረጥ አያይዛችሁ ድርብ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡ /ገፅ ፡103/ ትክክለኛውን አያያዥ ቃል በመጠቀም ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን ወደ ድርብ ዓረፍተ ነገር ቀይሯቸው፡፡

8ኛ ክፍልም እንዲሁ /ገፅ ፡14 /የሚከተሉትን ዓረፍተ ነገሮችን ስዋስዋዊ ስርዓቱን ጠብቃችሁ አስተካክላችሁ ፃፉ፡፡ /ገፅ ፡120/ ከዚህ በታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች የአወቃቀር ችግር ስላለባቸው አስተካክላችሁ በድጋሚ ጻፉ፡፡ መፃህፍት ውስጥ አብዛኛው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከላይ በገፁ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በተለያየ መንገድ ተደጋግመው የቀረቡት የተወሰኑ ናቸው፡፡ ይህ አቀራረብ ከቀረበው የሰዋስው ይዘት አንፃር ሲታይ ተከታታይነቱ ውስን ነው፡፡

በአንድ የክፍል ደረጃ የቀረበ የሰዋስው ይዘት በቀጣይ የክፍል ደረጃ መምጣቱን በተመለከተ በኦሮሚያ ክልል በተዘጋጀው የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የተማሪው መፃህፍት ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች 7ኛ ክፍል /ገፅ ፡ 66/ በዚህ ትምህርት ክፍል ስለ ባለቤት፣ተሳቢና ግስ የተመለከተ ማስታወሻና መልመጃዎች ቀርበውላችኋል፡፡ መልመጃዎቹን በትዕዛዛቸው

መሠረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ፡፡ 8ኛ ክፍል ቀጥሎ ከቀረቡት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ባለቤት፤ማሰሪያ እቀንጽና ተሳቢ ለይታችሁ በሰንጠረዥ ውስጥ አመልክቱ፡፡ በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች መካከል የቀረበው የስዋስው ይዘት ሲታይ ተከታታይነቱ ውስን መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ የይዘቶቹ ተከታታይነት በመርሀ ትምህርት ጋር በተስማማ መልኩ መደራጀቱ ተረጋግጧል፡፡

### 4.3.3.ተለጣጣቂነት

ተለጣጣቂነት የሰዋስው ይዘቶች እርስ በርሳቸው ተቆላልፈው በመሄድ የተማሪው የቋንቋ ደረጃ እያደገ በሄደ ቁጥር በመመሪያ መፃህፍት ውስጥ ያሉ ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት እያገኙ እንዲሄዱ የሚደረግበት ደረጃ እንዲሁም በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች መጀመሪያ ከቀረቡ የትምህርት ይዘቶች ተነስተው ስፋትና ጥልቀት እየጨመሩ መምጣትን የሚመለከት እንደሆነ በክለሳ ድርሣናት ላይ ተጠቁሟል፡፡

የ7ኛ ክፍል መጽሀፍ /ገጽ :54/ከዚህ በታች ጥንድ ጥንድ ሆነው የቀረቡን ዓረፍተ ነገሮች ከቀረቡት አያያዥ ቃላት በመምረጥ አያይዛችሁ ድርብ ዓረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

- እንጂ - ስለዚህ - ይሁን እንጂ - በመሆኑም

ምሳሌ፡ ማጥናት እፈልገለሁ፡፡

- ፀጥታ መኖር አለበት፡፡
- ማጥናት እፈልጋለሁ ስለዚህ ፀጥታ መኖር አለበት፡፡

8ኛ ክፍል የሚከተሉትን ነጠላ ዓረፍተ ነገሮችን በማጣመር ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

ምሳሌ፡- ሀ. ልጁ መጽሀፍ አሳተመ፡፡

ለ. ብዙ አድናቂዎች አገኘ፡፡

- ልጁ መጽሀፍ አሳተመ፤ በዚህም ብዙ አድናቂዎች አገኘ፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ምሳሌዎች የተለጣጣቂነትን መልክ የያዙ ቢሆንም በሁለቱም ተተኳሪ መጻህፍትም ሆነ በየምዕራፉ የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች መካከል ስፋትና ጥልቀት እየጨመረ የሄደ ይዘት የተወሰነ መሆኑና የተለጣጣቂነት ችግር ያላቸው መሆኑ ተረጋገጧል፡፡

## 4.4. መማሪያ መጻህፍቱ ከመረሀ ትምህርቱ ጋር ያላቸው ዝምድና

በኦሮሚያ ክልል የ7ኛና የ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርትና መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የቀረቡት ዝርዝር የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች፡ የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ-7፡ የ7ኛ ክፍል በመማሪያ መፅሀፍና በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት ዝርዝር የሰዋስው ይዘቶች

| ተ.ቁ. | የሰዋስው ይዘቶች | ክፍል<br>7ኛ | መርሀ ትምህርት | መማሪያ መፅሀፍ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ስሞችንና ግሶችን ከዓረፍተ ነገር መለየት | x | x | x |
| 2 | ቅድመና ድህረ  ግንድቅጥያዎችን ከቃል ግንድ መለየት | x | x | x |
| 3 | ስምና የስም ገላጭ መለየት | x | x | x |
| 4 | በዓረፍተ ነገር ውስጥ ያሉትን የቁጥር ስህተቶች አስተካክሎ መጻፍ | x | x | x |
| 5 | አያያዦችን በመጠቀም ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት | x | x | x |
| 6 | በዓረፍተ ነገር ውስጥ ባለቤት ፣ተሳቢና ግስን መለየት | x | x | x |
| 7 | የስም አይነቶችን መለየት | x | x | x |
| 8 | ስማዊና ግሳዊ ሀረጎችን መለየት | x | x | x |
| 9 | በዓረፍተ ነገር ውስጥ ያሉትን የፆታ ስህተቶች አስተካክሎ መፃፍ | x | x | x |

“X” መኖሩን ወይም ደግሞ አለ የምለውን ያመለክታል፡፡

ሠንጠረዥ- 8 ፡ የ8ኛ ክፍል በመማሪያ መፅሀፍና በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት ዝርዝር የሰዋስው ይዘቶች

| ተ.ቁ. | የሰዋስው ይዘቶች | 8ኛ ክፍል | መርሀ ትምህርት | መማሪያ መፅሀፍ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሰዋስዋዊ ህግን ያልተከተሉ ዓረፍተ ነገሮችን አስተካክሎ መጻፍ | x | x | x |
| 2 | በዓረፍተ ነገር ደረጃ ሰዋስዋዊ ምስረታን መጠቀም | x | x | x |
| 3 | ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን መለየት | x | x | x |
| 4 | ድምጾችን በማቀናጀት ትርጉም አዘል ቃላትን መመስረት | x | x | x |
| 5 | ዓረፍተ ነገር መመስረት | x | x | x |
| 6 | ባለቤት ተሳቢና ግስ ያላቸውን ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት | x | x | x |
| 7 | የቃል ክፍሎችን መለየት | x | x | x |
| 8 | ድርብ ዓረፍተ ነገሮችን መመስረት | x | x | x |
| 9 | ሰዋስዋዊ አገባባቸው የተዛቡ ዓረፍተ ነገሮችን ማስተካከል | x | x | x |
| 10 | በአግባቡ የተዋቀረ ቃል፣ሀረግ እና ዓረፍ ነገር መጻፍ | x | x | x |

“X” መኖሩን ወይም ደግሞ አለ የምለውን ያመለክታል፡፡

በዚህ መልክ የ7ኛና የ8ኛ ክፍል መርሀ ትምህርት ያካተታቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ለደረጃው በተዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ ብዙዎቹ ሳይደጋገሙ ጥቅቶቹ ደግሞ ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡ ስለዚህ መማሪያ መጻህፍቱና መርሀ ትምህርቱ ጥልቅ ትስስር አላቸው፡፡ በመርሀ ትምህርቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች በመማሪያ መጻህፍቱ ተካተው ይገኛሉ፡፡ ከላይ ባየነው መሠረት የ7ኛና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍትና መርሀ ትምህርቱ ስምምነት ያላቸው ናቸው ለማለት ያስችላል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳብ

## 5.1. ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋነኛ ዓላማ፣ በኦሮሚያ ክልል በ2015 ዓ.ም ስራ ላይ በዋሉ ለ7ኛና ለ8ኛ ክፍል የተዘጋጁ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት እንዴት እነደሆነ መፈተሽ ነው።ጥናቱን ከግብ ለማድረስ ታላሚውን መጻህፍት የሰነድ ምርመራ በማካሄድ የተገኙትን መረጃዎች በክለሳ ድርሳን ላይ መሠረት በማድረግ አይነታዊ የአተናተን ዘዴን በመጠቀም በገላጭ ስልት ቀርቧል።

በዚህ ዓላማ መሠረት የመማሪያ መጻህፍቱን ሰዋስዋዊ ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ለመፈተሽ የሚያስችል ንድፈ ሀሳቦችን በመመልከት ከጥናቱ ዓላማ ጋር የሚዛመዱ ፅሁፎችንና ጥናቶችን በመዳሰስ ለግምገማው የሚሆኑ መስፈርቶችን ለመምረጥ ተችሏል፡፡በመስፈርቶቹ መነሻነትም በዋናነት የሰነድ  ፍተሻ በማድረግ በአጋዥነት ደግሞ ለመምህራን የሚቀረቡ ቃለ መጠይቆችንና ተማሪዎች የሚሞሏቸውን የጽሁፍ መጠይቆች በማዘጋጀት ተፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

በተሰበሰቡ መረጃዎች የሰነድ ፍተሻው ላይ ትኩረት በማድረግ የቃለ መጠይቁን ከጽሁፍ መጠይቁ ምላሽ ጋር በማዛመድ ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡ በመጽሀፍቱ ውስጥ የተካተቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ከይዘት  ማቅረቢያ መስፈርቶች አንጻር ሲታይ አካሄዳቸው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብ የቀረቡ ሲሆን ከትኩረታቸው አኳያ በውጤት ተኮርና በሂደት ተኮር አቀራረብ የቀረቡ ናቸው፡፡

የ7ኛ ክፍል እና የ8ኛ ክፍል መጻህፍት አቀራረባቸው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆነ ዘዴ ሰዋስውን ለማስተማር የተለያዩ ይዘቶች በብዛት ቀርበዋል፡፡ በአመዛኙ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ ዘዴ የቀረበውን ገለጻ መሠረት አድረገው ህጉን እየተከተሉ የቀረቡትን ገለጻዎች በተለያየ መንገድ እነዲጠቀሙባቸውና ወደ ተግባር ቀይረው እየሰሩ እንዲለማመዷቸው የተመረጡ ቢሆንም በዚህ ስልት የቀረቡት ይዘቶች ግን ጥቅት ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉንም የማቅረቢያ መንገዶችን ቀላቅሎ ማቅረቡ ከጠንካራ ጎን የሚታይ ይሆናል፡፡

ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ከስነ-ትምህርታዊ ሰዋስው ማቅረቢያ መስፈርቶች አንጻር በርካታ ጠንካራ ጎኖችን ለማስተዋል ተችሏል፡፡ ሌሎቹ የሚከተሉት  ናቸው፡፡

በሁለቱም መማሪያ መጻህፍት ከቀረቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ውስጥ የተወሰኑት ድግግሞሽ የሚታይባቸው ሲሆን አንዳንድ ጊዜ ብቻ ታይተው የማይቀጥሉም እንዳሉ ማወቅ ተችሏል፡፡ ከተገቢነት አንጻር  በመማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ ከተማሪዎች እድሜ፣የእውቀት ዳራ፣የክፍል ደረጃ፣ፍላጎትና ዝንባሌ ጋር የማይስማሙ ይዘቶች መኖራቸው ተረጋግጧል፡፡

የትምህርቱ ይዘቶች ተከታታይነት ኖሯቸው ቢደራጁ የተማሪዎች ዕውቀት በማዳበር ረገድ ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡እንዲሁም ከተለጣጣቂነት አንጻርም የይዘቶች በአንድ ክፍል ወይም በተከታታይ የክፍል ደረጃ ተደጋግመው መቅረብ ተገቢ ቢሆንም ተደጋግመው የቀረቡ ይዘቶች የበለጠ ስፋትና ጥልቀታቸው እየጨመረ እንዲሄድ ቢደረግ አያስለችም ፡፡

## 5.2. የመፍትሄ ሐሳብ

በጥናቱ መሠረት ጠንካራ ጎኖች የበለጠ እንዲጠናከሩና ደካማ ጎኖች ደግሞ በቀጣይ ማሻሻያ እዲደረግባቸው የመፍትሄ ሀሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

- ተተኳሪ በሆኑ መማሪያ መጻህፍቱ ውስጥ የተካተቱ የሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር በሆነ መንገድ መቅረባቸው ጥሩ ሆኖ ሁለቱንም አቀራረብ አመጣጥኖ ማቅረብ ላይ ትኩረት ቢደረግ ተመራጭ ይሆናል፡፡
- ተተኳሪ መማሪያ መጻህፍቱ ሰዋስዋዊ ይዘቶቹ አብዛኛውን ትኩረት ያደረጉት ውጤት ተኮር መሆናቸው ሰዋስውን ተግባቦታዊ በሆነ ዘዴ መማር እንዳይቻላቸው ስለሚያግዱ ቀጣይ በሚዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መጻህፍት ላይ ተማሪዎቹ ኢ- አፈ-ፊት መሆናቸው ትኩረት ተሰጥቶ ማሻሻያ ቢደረግበትና ሁለቱንም ትኩረቶች በተናጥል ያሉባቸውን ክፈተቶች በማስቀረት ሁለቱንም አጣምሮ በማቅረብ ችግሩን ማስወገድ፡፡
- ቀጣይ የሚቀርበው መማሪያ መጻህፍና መርሀ ትምህርት የተማሪዎቹን ዳራዊ እውቀት ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ቢሆን ይመረጣል፡፡

አጠቃላይ በሆኑ የመማሪያ መጻህፍቱ መልክ ቅደምተከተላቸውን የጠበቁና ስፋትና ጥልቀትን እየጨመሩ የሚደራጁ ቢሆኑ ቀጣይ በሚዘጋጁ መማሪያ መጻህፍት ላይም ይህ ሁነታ ትኩረት ቢደረግ፡፡

## ዋቢ ጽሁፎች


ባየ ይማም፡፡ (1987) ፡፡የአማርኛ ሰዋስው፡፡ የተሸሻለ ሁለተኛ እትም፣አዲስ አበባ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

_______፡፡(2000)፡፡የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አድስ አበባ፣ እሌኒ ኃላፍነቱ የተወሰነ የግል ማህበር፡

ጌታሁን አማረ፡፡ (1987) ፡፡ ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡ አስረኛ እትም፣አዲስ አበባ፣አልፋ ማተሚያ ቤት፡፡

Batstone,R.(1994).*Grammar*. Oxford:Oxford University Press.

Brown, D. (1994). Principle of Language Learning and Teaching. USA: Pretice.Hall.

Bygate, M , Tonkyn, A, Williams, E. (1994). Grammar and Language Teacer. Hernel Hempstead: Prentice Hall.

Cunningsworth, A. (1984). Evaluating and Selecting EFL. Teaching Materials: Fifth print Oxford: Heinman.

_______. (1995).Choosing Your Course Boook: Oxford Heineman.

Dawnson, C. (1984).Teaching English as Foreign Language.Edinburgh: Nelson Harp.

Dubin, F. and E, Olshtain.(1986).Course Design.Cambridge:Cambridge University Press.

Ellis, R. (2000)."The Place of Grammar Instruction in second or Foreign Laguage Curriculum" In

Brown, K.(ed.)Language and Linguitics. Encyclopdia,Vol.9, Oxford: Eisevier Ltd

Greenbaun,S.(1986). "English and Grammarian's responsibility: the present and the future." World English, Vol 5, No 213.

Grant, N. (1978). Making the most of Your Text Book. London. Longman.

Harmer, J.(1987).Teaching and Learning Grammar. London: Longman.

Larsen-Freeman, D.(1991)." Teaching Grammar". In CeleMurcia, M. (ed.).Teaching

English as Second / Foreign Language.Boston. Heinman Publisher

_____. (1986).Teachniques and Principles in Language Teaching.Oxford: Oxford University press.

Mitchell, R.(1994) "Foreign Language Teachers and Teaching of Grammar."Bygate.M,

Tonkyn, A.and Williams,E.(eds).Grammar and Language teacer.Cambridge: Cambridge University Press.

Nunan, D. (1991). Language Teaching Methodology: A Tex book for Teacers.Oxford: International Book distribution Ltd.

Palmer, F. (1984) . Grammar (2nd ed.). New York: Penguin book.

Ruthford, W.C. (1987). Second Language Grammar. London : Lomgman.

Tonkyn, A. (1994). “Introduction; Grammar and Language Teacher”.In Bygate, M, Tonkyn,

A. and Williams, E. (eds) Grammar and Language Teacher.Cambridge: Cambridge University Press.

Tylor, R.W. (1949).Basic Principles of Curriculum and Instruction.Chicago: The University of Chicago Press.

Ur, P. (1988).Grammar Practice Activities.Cambridge: Cambridge University Press.

…………... (1996). A Course in Language Teaching . Cambridge. Cambridge University Press.

Woods, E. (1995). Introducing Grammar. Harmonds worth: Penguin.

# አባሪዎች

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ ቋንቋዎች ጥናት፣ጆርናሊዝምና ኮሚኒከሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ፅሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

**አባሪ -1 ፡- ለተማሪዎች  የተዘጋጀ የፅሁፍ መጠይቅ**

በ2014 ዓ.ም ኢ- አፊ ፊት ለሆኑ ተማሪዎች የተዘጋጀ የ7ኛ ና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት ውስጥ  የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት በመገምገም የመማሪያ መፃህፍቱን ጠንካራና ደካማ ጎን ለመለየት ነው። ለዚህም መጽሀፉን የሚማሩ ተማሪዎች አስተያየት አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል። ስለዚህ ለቀረቡት ጥያቄዎች የምትሰጡት ምላሽ ለጥናቱ አስፈላጊ በመሆኑ ተገቢውን ምላሽ እንድትሰጡ በአክብሮት እጠይቃለሁ።

ስም  መፃፍ አያስፈልግም።

1. የተማሪው አጠቃላይ መረጃ

ፆታ---------------- ዕድሜ------------- የትምህርት ቤት ስም-------------------------

ለቀረቡት ጥያቄዎች ሶስት ሶስት አማራጮች መልሶች ከጎናቸው ተቀምጠዋል ለጥያቄው መልስ ይሆናል የምትሉትን አማራጭ መልስ ስር (x) ምልክት በማድረግ መልሱ፡፡

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አልስማማም | ለመወሰን እቸገራለሁ | እስማማለሁ |
| 1. | በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ትምህርት መልመጃዎች ስትሰሩ በጣም የቀለሏችሁ ይዘቶች ነበሩ፡፡ | | | |
| 2. | በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው መልመጃዎች ስትሰሩ በጣም የከበዳቸው ይዘቶች ነበሩ፡ : | | | |
| 3. | ከቀረቡት ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካከል ከመስራት አቅማችሁ በላይ የሆኑ ገለፃ፣ምሳሌና መልመጃ አጋጥሟችኋል፡፡ | | | |
| 4. | አሁን በምትማሩበት መማሪያ መፅሀፍ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከባለፈው ክፍል የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ጋር ስፋትና ጥልቀት ጨምሯል፡፡ | | | |
| 5. | በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ ተደጋግመው ቀርበዋል፡፡ | | | |
| 6. | በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የቀረቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ካለፈው ትምህርት ይከብዳሉ፡፡ | | | |
| 7. | ካለፈው የክፍል ደረጃ ከተማራችሁ የሰዋስው ይዘቶች የተለየ አዲስ ከዚህ መፅሀፍ ተምራችኋል፡፡ | | | |

በመጨረሻም በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አስመልክቶ ያላችሁን አጠቃላይ አስተያየት ስጡ፡፡

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------------------------------

## አባሪ 2 ፡- ለመምህራን የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ

የመምህራን ሙሉ መረጃ

የሚያስተምርበት የክፍል ደረጃ----------------------------- የአገልግሎት ዘመን---------------------

የሰለጠኑበት የትምህርት መስክ------------------------------- የት/ደረጃ--------------------------------

1. በመማሪያ  መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ስያስተምሩ ግልፅ ያልሆኑ ገለፃዎች ፣ምሣሌዎችና መልመጃዎች አጋጥሞታል፡፡
2. በመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ ለመረዳት አስቸጋሪ የሆኑ ሰዋስዋዊ ይዘቶች አጋጥሞት ያውቃሉ?
3. ከተማሪዎች የመረዳት አቅም በላይ ወይም በታች የሆኑ ሰዋስዋዊ ይዘቶች አጋጥሞት ያውቃሉ?
4. በመማሪያ  መፅሀፉ ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡት የሰዋስው ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት ይታይባቸዋል?
5. በመማሪያ  መፅሀፉ ውስጥ የተካተቱት ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ስያስተምሩ ከከባድ ወደ ቀላል አልያም ከቀላል ወደ ከባድ የሚጓዝ ይዘት ገጥሞታል?
6. ከመማሪያ መፅሀፉ ውስጥ አንድ የሰዋስው ይዘት በተለያዩ ምዕራፎች ተደጋግሞ ሲቀርብ አስተውለዋል?
7. ከመማሪያ መፅሀፉ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ያሉትን ተጨማሪ አስተያየት ይግለፁ?